መስከረም 17ቀን 2011ዓም

# <u>አዲስ አበባም በነሌንጮ ክህደት እየተናጠች ነው?</u>

ከአርዕስቱና አዲስ አበባን አሥመልክቶ በተራ ቁጥር(1)ከተፃፈው ውጭ ያለው ጥር7 ቀን 2009ዓም የተፃፈና አሁን ያለንበትን ወቅታዊ ሁኔታ ይገልፀዋል በሚል የወጣ ነው።

ዛሬ ይህንን ፅሁፍ ለመፃፍ የገፋፉኝ ተያያዥ የሆኑ ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች **<u>አዲስ አበባና</u> ጠቅላላ** <u>የኦሮሞ የአገር ባለቤትነት ታሪክ</u> ናቸው።

በቅድሚያ እያንዳንዳችን ታሪካችንን በአግባቡ ብናነብና ብንረዳ ፣የሀሰት ታሪክ በሚከሰትበት ወቅት፣ማምከኛው በድርጅት መደራጀትና መመከት እንጅ፣በተናጠል መቃጠል መፍትሄ አይሆንም።

**ማሳሰቢያ**!ይህንን <u>ታሪክ አዘል</u> ፅሁፍ ያላንዳች መሰልቸት እሥከመጨረሻው እንድታነቡት እጋብዛለሁ።

(1ኛ) አዲስ አበባን አሥመልክቶ በቅርቡ አምሥት የኦሮሞ የዘር ድርጅቶች ማለትም <u>በ1983ዓም ህገ መንግሥቱን ከትነግ ጋር ያፀደቁት እነዲማ</u> <u>ነግዎና ሌንጮዎች</u>፣የ<u>መራራ ጉዲናና የበቀለ ገርባ</u> ድርጅት፣እንግሊዝ <u>ለንደን ውስጥ "**በኢትዮጵያ**</u> መቃብር ላይ<u> **ኦሮሚያን**</u> እንገነባለን" ሲል ተሰብሳቢዎቹ <u>እነጃዋር፣እነ እዝቄል</u> ያጨበጨቡለትና ብዙዎቻችንን ጉድ ያሰኘው<u> **ሊበን ዋቆ** </u>ያለበት <u>የእነገንፍ ድርጅት</u>፣ወዘተ...ያው የተለመደውን "የተጎዳንና የተናቅን፣የተጠላን ወዘተ"ለቅሷቸውንና ማላዘናቸውን ካሥደመጡን በኋላ <u>የአዲስ አበባ ባለቤት ኦሮሞ</u> እንደሆነና እኛ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ሆነን መብታችንን እነሱ ሊያሥጠብቁልን እንደሚችሉ ፊት ለፊት በድፍረት መግለጫ በማውጣት አፈረጡት እንጅ፣ተንኮሉ የተሰራው በእነ መለስ ትነግና በእነሌንጮ ኦነግ በ1983ዓም ግንቦት ወር አማራው የተገለለበትን የሽግግር መንግሥት ሲያቋቁሙ ነው።

ይህ በበታችነት በሽታ በሚሠቃዩት በአማራ ጠሎቹ በእነመለስ ትነግ እና በእነሌንጮ ለታ|ዲማ ነግዎ| |ዳውድ ኢብሳ| አባ ቢያ (ኦነግ) ተባባሪነትና አርቃቂነት <u>ዘርና ቋንቋን መሠረት በማድረግ</u>

(ሀ)<u>የኢትዮጵያን አንድነት</u> በማጥፋት፣<u>በዘር</u> በተከፋፈሉ በዘጠኝ(9)መንግሥታትና ባንዲራዎች በመተካት፣

(ለ)የ<u>ነባሯን የኢትዮጵያ የማንነት ካርታን </u>በመለወጥ፣<u>በዘር</u> በተሸነሸነች አዲስ ካርታ በመተካት፣

(ሐ)የነፃነታችንን ሡንደቅ ዓላማ አሽቀንጥረው በመጣል፣ በተግባር የብሔሮችንና የሃይማኖቶችን እኩልነት ሳይሆን በዘር ተለያይቶ መጠፋፋትን ባመጣልን በሌላ ባንዲራ በመተካት፣

(መ)ትነግና ኦነግ! "ለወደፊት ሁኔታው ካላመቸን" በሚል ቀደም ሲል የተነሱበትን መገንጠል "ህጋዊ ሽፋን" ለማላበስ ይረዳቸው ዘንድ አንቀፅ 39ኝን በህገ መንግሥት ተብዬው በማካተት አፀደቁ።

የተለያዩትንም ነገዶች በክልል የሸነሸኗቸው ለነገዶቹ ጥቅም አስበው ሳይሆን፣ለእኩይ ተግባራቸው በመንገዳቸው ላይ በመቆም እንቅፋት ይሆናል ብለው፣ በጠላትነት የፈረጁትን አማራ ኅልውናውንና ቋንቋውን ከጊዜ ጋር አዳክሞ ለማጥፋት፣ እንዲሁም የሚቀራመቱትን መሬት ቋሚና የተረጋገጠ ዋስትና እንዲኖረው ለማድረግ " በአገሪቱ ውስጥ ለደረሱት ሁሉ ችግሮች በዳይና ጨቋኝ፣የኢትዮጵያ ሀገራዊና ህዝባዊ አንድነት በሚል የቆሙትና የብሔሮችን እኩልነት የማይቀበሉት ትምክህተኛ አማሮች ናቸው" ብሎ በመስበክ፣ ነገዶቹ ከጎናቸው እንዲቆሙና በአማራው ላይ እንዲዘምቱበት ለማሥቻል ነበር። ይህም እሥካሁን ከሞላ ጎደል ተሳክቶላቸዋል።ፍፃሜው ግን አይደለም።
***ትህነግ እና የእነሌንጮ ኦነግ***! የመጀመሪያው የአማራ ማዳከሚያ ያደረጉት ነገር ቢኖር "ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ" እንዲሉ፣ አማራው የሚኖርባቸውን አካባቢዎችና መሬቶች በጉልበታቸው በመቀራመት ፣የዝሆኑን ድርሻ መሬቶች መውሰድ ነው።ይህ አዲስ አበባንም ይጨምራል።

***ይህ*** ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የተተከለው መርዝ ከርሥት ከመሬት መፈናቀል አንሥቶ መላ አገሪቱን ውሥጡን ውሥጡን እንደምሥጥ ሲበላና በሚሊዮኖች የሚቆጠር የሰው ህይወት ሲቀጥፍ ኖሮ ዛሬ አዲስ አበባ ላይ ገሀድ ወጣ።እንኳን አዲስ አበባ ጠቅላላ ኢትዮጵያም የዘር ክልል ፈርሶ የሁሉም መሆኗ አይቀሬ ነው።

እነዚህ በጠባብ ጎሰኝነት የተለከፉ ድርጅቶች ይህ የውሸት ታሪክ በተደጋገመ ቁጥር እየታመነና ተቀባይነት እያገኘ ይሄዳል የሚል ዕምነት አላቸው። ይህ ደግሞ አይሆንም አይባልም፣በኤርትራ ሆኖ አይተነዋልና። የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት እንዳልነበረ እየታወቀ፣ እነኢሳያስ የቅኝ ግዛት ነው ብለው ብዙ ዓመታት ገፉበት፣ ውሸት ሲደጋገም ህልም አይሉት ቅዠት ዕውነት መሥሎ እዛሬው ዘመን አድርሶናል።

ከእንግዲህ ምርጫችን ተደራጅቶ መመከት ብቻ ነው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ የአቢይንም ሆነ የሌላ ሰው ፈቃድ አይጠይቅም።በተግባር ሲታይ ዶክተር አቢይ መንታ ምላስ ይዞ መንታ መንገድ ላይ የቆመና አማራውም ሆነ የአንድነቱ ሃይል የየራሳቸውን ትግል አቀዝቅዘው፣ የአቢይን መንግሥትና የኦሮሞን ትግል አጅበው ሥልጣኑን እንዲያጠናክሩለት የሚሻ ይመሥላል።

(2ኛ)ኦነግ ከወያኔ ጋር ሲሰራ በተለያዩ አካባቢዎች በአማራው ላይ ሥለፈፀመው ወንጀል ሌንጮ ለታ ተጠይቆ "በደኖም በሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ያደረገው እንጅ ኦነግ አይደለም፣አርባጉጉም ኦህዴድ እንጅ እኛ አላሥተዳደርንም" ብሎ የሰጠው አሥገራሚ መልስ ነው።

እንዲህ ዓይነቱ አሥገራሚ የታሪክ ክህደትም "አሣ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል" እንደሚባለው፣ ቀደም ብሎ <u>በ16ኛው ክፍለ ዘመን በኦሮሞ የተደረገውን ወረራ በጥልቀት እንድንቃኝ</u> እንገደዳለን። እሥከዛሬ እንደታየው ሽፍጥንና ክህደትን በቀጣይነት ካሥተናገድን፣ የበለጠ እየጎዳንና ከምድረገፅ እያጠፋን ይሄዳል፣ዕውነትን ከተጎናፀፍን ግን በመካከላችን የመተማመን ብልጭታ ሊከሰት ይችል ይሆናል።

ዛሬ ኦነግ በአማራው ላይ የፈፀመውን እንዳልፈፀመ የሰነዘረው አነጋገር ከኤርትራው ክህደት ያልተለዬ ከዕውነት የራቀ ሥለሆነ፣ **"ሌንጮና ማሥረጃዎች"** በሚለው ፅሁፍ ሥር ይመልከቱ።

ይህ ፅሁፍ የተሟላ የሚሆነው ከግራኝ ሲጀመር ነው።

**<u>በመጀመሪያው</u>** ክፍል **<u>አህመድ ኢብራሂም ኤል ቃዚ(ግራኝ አህመድ)</u>** በቱርኮች እየተረዳ ባደረሰው የጥፋት ዘመቻ የአማራ ሕዝብ ለሀገሩ ነፃነትና ለሀይማኖቱ መጠበቅ የከፈለውን መስዋዕትነት ባጭሩ ይገልፃል።ይህ በግራኝ ወረራ የደቀቀ የአማራ ሕዝብ፣ በቀጣዩ የጋላ(ኦሮሞ) ወረራ ይበልጥ ደቋል።

**<u>በሁለተኛ</u>** ክፍል ***<u>ጋሎች(ኦሮሞዎች)ወደኢትዮጵያ የገቡበትን ጊዜና ሁኔታ</u>*** ይዳሥሣል።

**<u>በሦሥተኛው</u>** ክፍል ***<u>ግራኝ አህመድ በቀደደው በር</u>***፣ የአገሪቱን ሀብትና የሰው ኃይል ባሚጠጠበትና የአስተዳደሩን መዋቅር ባወደመበት ማግስት አጋጣሚውን በመጠቀም ***<u>"የኦሮሞ ወረራ"</u>*** ተካሄደ።ከወረራው በፊት ዛሬ "የኦሮሚያ ምድር" በተባለው አካባቢ የነበሩትን ነባር የኢትዮጵያ ነገዶች ይዘረዝራል።የቱ ሕዝብ በምን ወቅት በየትኛው ቦታ እንደነበር እንመለከታለን።ይህም ሲባል ዛሬ እንለይ የሚሉን ኃይሎች አቋማቸውን አሥተካክለው አብሮነትን ከተቀበሉ ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮ በመኖር ዘመናትን ያሳለፈና የተዋሀደ በመሆኑ አንዱ ነገድ ከሌላው ይልቅ የበለጠ የባለአገርነት መብት አለው አንልም፣ ካላስተካከሉ ግን ተቃራኒውን ከመተግበር ውጭ አማራጭ የለም።።

***<u>አራተኛውና</u>*** የመጨረሻው ክፍል ***<u>የኦሮሞ ነፃነት ግንባር(ኦነግ)</u>*** የኢትዮጵያን አንድነት ለመናድ፣የአማራና የኦሮሞን ሕዝብ ለማጨራረስ ሥለአቀነቀናቸውና ሥለሚያቀነቅናቸው ታክቲኮችና"መጤ ሕዝቦች"ብሎ የሚጠራቸውን፣ የማፈናቀልና የማጥፋት ተግባሩ

ቢቀጥልና ሙሉ በሙሉ  በሥራ ላይ ቢያውል ሊያስከትል የሚችለውን ትልቅ ችግር ለማሳዬት ይሞክራል።

## <u>ክፍል1</u>                    <u>የግራኝ አህመድ ወረራ</u>

አህመድ ኢብራሂም ኤል ቃዚ  አጋዴን ውስጥ በምትገኝ ሆባት በምትባል መንደር  በአባቱ “መለሳይ” በእናቱ “ሐርላስ” ከተባሉ የሶማሌ ጎሳዎች በ1498ዓ.ም የተወለደ የጦር መሪ ነበር።

በግራኝ ወረራ ዋዜማ የኦቶማን ቱርክ የዘመኑ የአካባቢው ኃያል መንግሥት ሥለነበረች ግዛቷ እሥከ ምሥራቅ አውሮፓ ሰሜንና ምሥራቅ አፍሪካ እንዲሁም የአረቡን ዓለም በሙሉ የሚያጠቃልል ሲሆን የቱርክ የንግድና የጦር መርከቦች የሜድትራንያንንና የሕንድ ውቅያኖስን ይቆጣጠሩ ነበር። አገሮች የወረረችበት ዋና ምክንያቶቿ (1ኛ) ግዛት በማስፋፋት የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመመዝበርና (2ኛ) የእሥልምና ሀይማኖትን ለማስፋፋት ነበር። በወቅቱም ከአካባቢው አገሮች ሁሉ  በቱርክ እጅ ያልወደቀች ኢትዮጵያ ብቻ ነበረች።

ደዋሮ(ሐረር) ውስጥ የነበሩ ኃያል የእስላም መሪዎች አቅም ሲያንሳቸው ለኢትዮጵያ ነገሥታት ታማኝ ሆነው በመገበር ሰላም ይፈጥሩ ነበር። በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመን ሲኖሩ የቱርክ መሣሪያና ወታደራዊ እርዳታ በገፍ ይመጣላቸው ጀመር።በዚህ ወቅት ነው አህመድ ኢብራሂም(ግራኝ) የተነሳው።

የቦታዎችን የጥንት ሥሞች በመጨረሻ ገፅ ይመልከቱ! የፈጠጋርን(አርሲ) አውራጃ ያስቸግር የነበረውን የእስላም ጦር በማሸነፍ ደገልሀን የተባለ የጦር መሪ እሥከ ሆባት አባረረው። ሆኖም ሆባት ላይ ሲደርስ የሥንቅና የትጥቅ እጥረት በደረሰበት ወቅት የግራኝ አህመድ ጦር መልሶ አባረረው።

በዚህም ግራኝ በ**1517**ዓ.ም.በንጉሱ በልብነ ድንግል ጦር ላይ የመጀመሪያውን ድል አገኘ። ይህም የመሣሪያና የወታደር እርዳታ ከቱርክ መንግሥት አስገኘለት።

በ**1521** ዓ.ም. የካቲት ወር ማለቂያ ላይ የግራኝ ጦር በሥውር ተጉዞ ሞጆ ወንዝ አካባቢ ከምትገኝ ባደቄ ከምትባል ሥፍራ ላይ ከንጉሱ ጦር ጋር ገጥሞ በመሸነፉ ሸሽቶ ዝቋላ ተራራ አጠገብ መሸገ። የንጉሱ የጦር መሪዎች ተከታትለው ሊደመሥሡት ሲችሉ ይህን ባለማድረጋቸው ግራኝ ሲጠብቃቸው የነበሩ ሁለት መቶ(200) የቱርክ ወታደሮች እሥኪደርሱለት ጊዜ ሰጡት።የአገሬው ኑዋሪዎች የነበሩት ሜያዎች ሊወጉት ሞክረው 300ቀስተኞችን ግራኝ ጨረሳቸው።

በዚያው ሳምንት እዚያው ዝቋላ አካባቢ “ሽምብራ ኩሬ” የተባለችውን ቀበሌ ለጦር ምሽግ ግራኝ መርጦ ያዘ።የጠበቃቸውም የቱርክ 200 ነፍጠኞች ደረሱለት።

**መጋቢት 3ቀን 1521**ዓ.ም. የሽምብራ ኩሬ ጦርነት ተደረገ።ከዚያን በፊት በኢትዮጵያ ታይቶ የማይታወቅ የጠመንጃ ጦርነት ታዬ።ይህ ለንጉሱ ወታደሮች ፍፁም አዲስ የሆነ የጦር መሣሪያ ለግራኝ ድል አሥገኘለት።በጦርነቱ 12000 ክርስቲያን ወታደሮችና 6000 የእስላም ወታደሮች እንደሞቱ፣በዕለቱ ከግራኝ ጋር አብሮ የነበረ አብድልቃድር የተባለ የአረብ ፀሀፊ ዘግቧል።

በአካባቢው የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጠሉ።ወንዶች አንገታቸው በሰይፍ ተቆረጠ። ሴቶችና ሕፃናት ወደአረብ አገር(የመን) ለባርነት ተላኩ።ከብቶች ወደሶማሊያ አገር ተነዱ። ጠንክሮ ለመመለስ ግራኝ በምርኮ ያገኘውን ይዞ ወደሐረር ተመለሰ።

**በሐምሌ ወር 1521**ዓ.ም. እንደገና ተመልሶ ደዋሮን(ሐረርን) ወረረ።ቀጥሎምባሊን(ባሌን) ወረረ።በባሌ የነበሩና የኖሩ ገዳማት ሀብታቸውና ወርቃቸው ተዘርፎ ተቃጠሉ።ከባሊ(ባሌ) ገዳማት በተገኘው ብቻ ሰባት(7) መድፎችንና ለሠራዊቱ የሚያስፈልገውን ስንቅና ጠምንጃዎችን ገዛ።ባሌ ውስጥ የወደሙ ገዳማት እሥከዛሬ አልተተኩም።

**በጥር ወር 1522**ዓ.ም. ግራኝ ጦሩን በይፋት በኩል አዝምቶ አንፆኪያ ላይ ታላቅ ጦርነት ተደረገ።የኢትዮጵያ ወታደሮች አይተውት በማያውቁት በመድፍ ጥይት ተደበደቡ። የደረጀችው የአንፆኪያ ቤተክርስቲያን በወርቅና በብር የተሰሩ ንዋዬ ቅድሳት በግራኝ የሶማሌ ወታደሮች ከተመዘበረ በኋላ እሳት ተለቀቀባት።

ግራኝ በወረራ በያዛቸው በደዋሮ(ሐረር) እና በፈጠጋር(አርሲ) አውራጃዎች የራሱን ሰዎች በመሾም ሥልጣኑን አደላድሎ በአዋሽና በዝቋላ መካከል  በሚገኘው በሜያዎች አገር ሰፈረ። በአካባቢው በመዘዋወር ብዙ ክርስቲያኖችን በሰይፍ እያስፈራራ አሰለመ።

**ሐምሌ 9ቀን 1523**ዓ.ም. በ1200ዓ.ም. የተመሠረተውን የታላቁን  የደብረ ሊባኖስ ገዳም ንብረት ካስመዘበረ በኋላ ከነመነኮሳቱ አቃጠለ።

ንጉሡ ልብነ ድንግል ግራኝን መቋቋም ሥላቃታቸው በሸሽት ወደቤተአማራ ተጓዙ።የግራኝ ዋና እቅድ ንጉሡን በመግደል ወይም ቢቻል ይዞ በማስለም ኢትዮጵያን በአጠቃላይ ለማስለም ነበር።ዱካቸውን ተከትሎ አንጎት(ራያ) ላይ ደረሰባቸው።ብርቱ መከላከል አድርገው ለጊዜውም ቢሆን ግራኝን ማቆም ተቻለ።

እዚያው አንጎት ውስጥ ግራኝ ንጉሱን ደርሶባቸው፣ንጉሱ ሲያመልጡ ሚናስ የተባለው የንጉሱ የመጨረሻ ልጅና ወዛዝርት በምርኮ ግራኝ እጅ ገቡ። ሁሉም የመንን ሲያስተዳድር ለነበረው የቱርክ ፓሻ በባርነት ተላኩ።አልሠልምም ያለውን የአንጎትን(የራያን) አማራ ሕዝብ ግራኝ በገፍ ጨረሰ። ቀጥሎም ወደ ጣና ሐይቅ በመሄድ በሐይቁ ደሴት ውስጥ የሚገኘውንና በ1200ዓ.ም. የተሠራውን ገዳም ሊያቃጥል ሲል መነኮሳቱ ገዳሙን ከቃጠሎ ለማዳን ባደረጉት ሥምምነት የገዳሙን ንብረት በጀልባ እየጫኑ አሥረከቡ።150ሰዎችን ለመጫን የተሠራ ጀልባ 3 ጊዜ ተመላልሶ ኣጋዘ።ከንብረቱ ውስጥ የወርቅ መስቀሎች፣ማጠኛዎች፣ ፅዋዎችና የከበሩ ዕቃዎች ይገኙበታል።

ግራኝ ይዞታውን ለማጠናከር ከባሕር ዳር እንደገና ወደ ደቡብ ምዕራብ በመምጣት የጦር ሠፈሩን እንደገና ወደዝዋይ አዛወረ።የአገሬው ኑዋሪዎች የሆኑትን የንጉሱን ታማኝ ዜጎች(የሜያ ሕዝብ) ከጠራረገ በኋላ ደዋሮን ቀጥሎም ባሌን  እንደገና ወረረ።

ግማሽ ቀን በፈጀው በዚህ በባሌ ጦርነት አዝማች አዳሉና ልጁ ዘመንክርም በታላቅ ጀግንነት ተዋግተው ከ3000የክርስቲያን ወታደሮች ጋር ወድቀዋል።

**በ1524**ዓ.ም. ምሥራቅ ደቡብና መካከለኛ የኢትዮጵያ ግዛቶች በግራኝ ጦር ተደብድበዋል።

በዚህ ዘመን ያልተወረሩ ግዛቶች ዳሞት(ጎጃምና ሌቃ(ምሥራቅ ወለጋ))፣ ቢዛም(ቄለም(ምዕራብ ወለጋ))፣ሰሜን ቤጌምድር፣ትግሬና ባሕር ምድር(ኤርትራ) ሥለነበሩ እነዚህን ግዛቶች ለመውረር እንዲችል **በመጋቢት 1525**ዓ.ም.ግራኝ  ሠራዊቱን ደብረ ብርሀን ላይ አከማቸ።በአጼ ዘርዐ  ያዕቆብ በተሠሩ ገዳማት ምትክ መስጊዶች ተሠሩ፣በግዳጅ የሰለመ ሠለመ፣ያልሰለመ የአካባቢ አማራ በግራኝ ሠይፍ አንገቱ ተቀላ፣ያመለጠውም ጫካ ገባ።

**በ1525ዓ.ም. መጨረሻ** ደምቢያንና አካባቢውን ከወረረ በኋላ በእንደርታ ላይ አልፎ ተምቤንን ወጋ።በሹም አጋሜ የተመራው ጦር ተምቤን ላይ ብርቱ መከላከል ቢያደርግም ግራኝን ማቆም አልቻለም።በዕለቱ ጦርነትም 10 000 የአጋሜ ወታደሮች አልቀዋል።

በዚሁ ዕለት አጼ ልብነድንግል አክሱም ገብተው ጦር ለማሰባሰብ ሞክረው ነበር፣ነገር ግን ግራኝ ሥለደረሰባቸው ወደ ወልቃይት ጠገዴ ሸሽተው አመለጡ።ግራኝም የአክሱምን ደብሮች ከእነቀሳውስቱ አቃጠለ።ቀጥሎም ሠራዬንና ቤጌምድርን ወረረ።

**በ1531**ዓ.ም ለረጅም ዘመን ሲጠበቅ የነበረው 1000ነፍጥ፣1000 የፈንጂ ጦር፣4 ከባድ መድፎችና በድምሩ **535ወታደሮችን** የያዘው በክርስቶፎር ደጋማ የሚመራው የፖርቱጋሎች

የጦር  ዕርዳታ በባሕረ ነጋሽ ይሥሐቅ መንገድ መሪነት ደብረ ዳሞ ደረሰ(ዝርዝሩን ለማወቅ "የፖርቱጋሎች ጀግንነት" የተባለውን መፅሐፍ ይመልከቱ)።

**ጳጉሜ 3ቀን 1532**ዓ.ም. አጼ ልብነ ድንግል ተሸሽገው ከኖሩበት በደብረ ዳሞ ደብር ሞቱ። ልጃቸው ገላውዲዎስ ነገሠ።

**ሚያዝያ 9ቀን 1534**ዓ.ም. **እንጣሎ** አጠገብ በተደረገው ጦርነት ለመጀመሪያ ጊዜ ግራኝ በጥይት ቆስሎ ተሸንፎ ሸሸ።

ዞብል በምትባል የደንከል በርሀ መንደር ገብቶ ጦሩን ማጠናከር ጀመረ።ከአለቆቹ ከቱርክ ገዥዎች ጋር በመላላክ በእጁ ያስገባው የክርስቲያን አገር ከእጁ ሊወጣ ሥለሆነ ወታደርና መሣሪያ ባስቸኳይ እንዲደርስለት ገጸ በረከት ጨምሮ ላከ።

ከቱርክ መንግሥትም 900 ምርጥ ነፍጠኞችን ያካተተ 2000ወታደሮችና 10 መድፎች ተላኩለት።

ለፖርቱጋሎች ምንም ዓይነት እርዳታ እንዳይደርስ የቱርክ መርከቦች ምፅዋንና አካባቢውን አጥረው ያዙ።ምንም እንኳን የሰውና የመሣሪያ እርዳታ ባይደርስለትም ክርስቶፎር ደጋማ ከግራኝ ጋር ለመዋጋት ቆረጠ።

**መስከረም 2ቀን 1535**ዓ.ም. **ዋግ** ላይ በተደረገው ውጊያ ኢትዮጵያውያንና ፖርቱጋሎች ብዙ ዕልቂት ደርሶባቸው ተሸነፉ።ክርስቶፎር ደጋማንም ግራኝ አንገቱን ቆርጦ ገደለው። ከፖርቱጋሎች ከ535ወታደሮች ውስጥ **150**ብቻ ነው የተረፉት።ግራኝም በድል አድራጊነት ኑሮውን ለመቀጠል ወደ ደምቢያ ሄደ።

ሸዋ ውስጥ ከግራኝ የጦር አለቆች ጋር ሲዋጋ የቆየው አጼ ገላውዲዎስ የግራኝን ከበባ ጥሶ ወደሰሜን በመምጣት ከተረፉት የፖርቱጋል ወታደሮች ጋር ተገናኝቶ በጋራ ሥለሚያደርጉት ጦርነት ተማክረው ዕቅድ አወጡ።

**በየካቲት ወር 1535**ዓ.ም.ገላውዲዎስ 9000ወታደሮችን ይዞ፣ግራኝ ደግሞ 15000ወታደሮችን አሰልፎ ደምቢያ ወረዳ ውስጥ ለሳምንት ያህል ተፋጥጠው ቆዩ።

**ረቡዕ የካቲት 28ቀን 1535**ዓ.ም. ሲነጋ **ዘንተራ በር** ከተባለው ሥፍራ ጦርነቱ ተጀምሮ ከብዙ ዕልቂት በኋላ የግራኝ ጦር ተሸነፈ።ግራኝም ተገደለ።ከግራኝ ጦር ውስጥ በህይወት ተርፈው ያመለጡ ሚስቱ ድል ወንበራና 40 የቱርክ ወታደሮች ብቻ ነበሩ።

<u>የግራኝ ወረራ ውጤት</u>

ሀ) የኦቶማን ቱርክ በኢትዮጵያ ላይ የመስፋፋት ዕቅድ ከግራኝ ጋር ዘንተራ በር (ደምቢያ) ላይ አብሮ ሞተ።

ለ) በዚህ ጦርነት የሌሎች ነገዶች  መስዋዕትነት ባይናቅም በባሊ፣በፈጠጋር፣በቤተ አማራ፣ በቤጌምድርና በዳሞት በብዛት የረገፈው የአማራ ሕዝብ ነው።

ሐ) ጦርነቱ የተካሄደው በራሷ በኢትዮጵያ ሀብት ነበር።በዚህ ጦርነት ምክንያት የኢትዮጵያ ሀብትና ንብረት የቱርክንና የየመንን ባለሥልጣናት እሥከተራው ወታደር ድረስ አክብሯል። የኮንስታንቲኖፐል ቤተ መንግሥት ዕቃዎች በወርቅ የተሠሩ እሥከመሆን ደርሰዋል።

መ)ምንም እንኳን አጼ ገላውዲዎስ በግራኝ ላይ ድል ቢቀናጅም በአካባቢው ግራኝ የሾማቸውን መሪዎች ለመምታትና አካባቢውን ለመቆጣጠር የረጅም ጊዜ ሥራ ሆነበት።አፄ ገላውዲዎስ ከግራኝ የእህት ልጅ ከኑር ዓሊ ጋር ሲዋጋ ሞተ።በዚህ ወቅት አገሪቱ በጦርነት የደቀቀች በመሆኗ "ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል" ሆነና <u>ለጋሎች(ኦሮሞዎች) ወረራ</u> የተጋለጠች ሆነች።

## <u>ክፍል2</u> <u>ኦሮሞዎች ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት ጊዜና ሁኔታ</u>

ጋሎች (ኦሮሞዎች) ከ10ኛው ክፍለ ዘመን በፊት ጀምረው ዛሬ የሶማሌ ግዛት በሆነው በበርበራ አካባቢ ይኖሩ እንደነበር በአርኪዎሎጂስቶች የሰው ዘር አመጣጥ ጥናቶች ተረጋግጧል።በዚህ ሥፍራ መቼና ከየት እንደመጡ በማስረጃ የተረጋገጠ ነገር የለም።

በ10ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ (ከ937ዓ.ም ወዲህ)የሱማሌ ነገድ ከታጁራ ባሕረ ሰላጤ ተነስቶ ጋሎችን(ኦሮሞዎች) ስለወጋቸውና ሥላሸነፋቸው ፣ከሚኖሩበት ከሰሜን <u>ሶማሌ</u>(ከእንግሊዝ ሶማሌ) <u>ከጋርዳይፋ ሠፈር</u> ለቀው በሽሽት ወደ <u>ደቡብ ምዕራብ</u> ተሰደው <u>በዋቢ ሸበሌና በጁባ ወንዞች</u> መካከል በ<u>ቤናድር</u> ሰፈሩ።ይህም ሥፍራ ሞቃዲሾ የሚገኝበትን የቤናድር አውራጃ ይዞ እሥከ ደቡባዊ የባሌ የቆላ አውራጃዎች ይደርሳል።በዚህ ሥፍራ ሲኖሩ ከውጭ ሕዝብ የሃይማኖትም ሆነ የንግድ ግንኙነት የሌላቸው ዘላኖች ነበሩ።ሥለዚህ ክርስቲያኖችም እሥላሞችም አልነበሩም።

ከጊዜ በኋላ ባንቱ የተባለ ኃያል ነገድ ከቤናድር አሥወጣቸው።ሰላምና የግጦሽ መሬት ፍለጋ ጉዟቸውን ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ  በመቀጠል በሲዳሞ ክፍለ ሀገር ውስጥ ቦረና ነገሌና አባያ ሐይቅ አካባቢ_ከሚገኘው ራሳቸው "ወላቡ" ብለው ከጠሩት ሥፍራ ሰፈሩ። ወላቡ ለከብቶቻቸው ግጦሽና ውሀ እንደልብ የሚገኝበት ከቤናድር ምድር ሲወዳደር ለምለምና ነፋሻ ሥፍራ በመሆኑ ብዙ የሙገሳና የምሥጋና ዘፈን ዘፍነውለታል።ለረጅም ዘመን ያለጦርነት በሰላም  ኖሩበት።የግጦሽ መሬትም እየጠበበ መጣ።የነገዱን ችግር

ለመፍታት “ገዳ” የተባለውን አስተዳደርን፣አምልኮንና ጦርነትን የሚመራ ሥራአት አቋቋሙ።(ሥለገዳ ሥራዓት በይበልጥ ለመረዳት አቶ ይልማ ደሬሳ በ1956ዓ.ም. ያሳተሙትን “የ16ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ”መፅሐፍ ይመልከቱ)።

## <u>ክፍል3</u> <u>የኦሮሞ ወረራ</u>

**በ1500ዓ.ም.** አካባቢ (1ኛ) ወላቡ በመጥበቡ (2ኛ) የድሮ ጠላታቸው የሶማሌ ነገድ በባሌ ቆላዎች በኩል እየመጣ ጥቃት ሥለሚያደርስባቸው ከወላቡ ተነስተው መሃል ኢትዮጵያን ለመውረር አሰቡ።

**በ1506ዓ.ም.** ከወላቡ ወደሰሜን ጥቂት በመግፋት <u>“አዳ ነቤ”</u> ብለው እሥከሰየሙት ቦታ ድረስ መጥተው ቆሙ።

ሆኖም **በ1508ዓ.ም.** የኢትዮጵያ ንጉሥ በአዳል ወራሪዎች ላይ ያገኘውን ድል ሲሰሙ በመፍራት ከወረራው ተቆጥበው በነበሩበት አካባቢ በትዕግሥት ቆዩ።

**ከ1517-1535ዓ.ም.** አማራዎችና ግራኝ በጦርነት ሲጨራረሱ ኦሮሞዎች የጦርነቱን ውጤት ይጠብቁ ነበር።ግራኝም አሸነፈ፣ንጉሱም አሸነፉ ኦሮሞዎች ግዛታቸውን ለማስፋፋት ከተዳከመ ጦር ጋር ቢጋጠሙ እንድሚሻላቸው ተገንዝበዋል።

ኦሮሞዎች ወላቡ በነበሩ ጊዜ በአራት ዋና ዋና ነገድ የተከፈሉ ነበሩ።እነሱም **ከረዩ፣መጫ፣ ቱለማና ወሎ** ናቸው።እያንዳንዱም ነገድ በስሩ ብዙ ጎሣዎችን ያቀፈ ነው።

ግራኝም ሆነ ንጉሱ የኦሮሞዎችን አባያ አካባቢ መሥፈር የሚያውቁ አይመሥልም። ቢያውቁም ይህን ያህል ለጦርነት የሚዘጋጅና የሚደራጅ ኃይል አልመሰላቸውም።

ኦሮሞዎች ወላቡና አዳ ነቤ በነበሩ ጊዜ የነበራቸው “ለፎ” የሚባል እግረኛ ጦር ብቻ ነበር። ወረራቸውን በስፋትና በብዛት እንዲሆን ሲያቅዱ የፈረሰኛ ጦር መመልመልና ማሰልጠን ጀመሩ።

ግራኝ ሲሸነፍ ገላውዲዎስ በየአውራጃው አሥተዳደሩን ለማረጋገት ቢሞክርም የንጉሱ ጦርም ሆነ አሥተዳደር በየአቅጣጫው የተዳከመ ነበር።

**በ 1535**ዓ.ም. መጨረሻ የከረዩ ነገድ የሆነው <u>በሜልባ ገዳ</u> አሥተዳደር የሚመራው <u>የጃዊ ጎሳ</u> የዊብን ወንዝ ተሻግሮ ደቡብ ባሌን ወረረ።የወረራው ዋና ዓላማ በደቡብ ኢትዮጵያ አውራጃዎች ላይ ሠፊ የመሥፈሪያ ቦታ ለማግኘት ነበር።ባሌን ለመከላከል ሀመልማል የተባለ የንጉሱ ሹም “በትረ አሞራ” የተባለውን ጦር ይዞ ከጃዊዎች ጋር ሲዋጋ ሞተ፣ጦሩም ወደሰሜን ባሌ ሸሸ።ጃዊዎችም ጦርነቱ ቢቀናቸውም የዘረፉትን ይዘው ወደ ወላቡ ተመለሱ

እንጅ ሰፍረው አልቀሩም።ሆኖም ለወደፊቱ በወረራ ብዙ ቦታ መያዝ እንደሚቻል ግንዛቤ ሠጥቷቸዋል።

**በ1536**ዓ.ም.ሁለተኛው የባሊ(ባሌ) ወረራ በሙደና ገዳ አሥተዳደር በሚመራው በበርቱማ ጎሣዎች ተደረገ።ከኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ይህን ወረራ የሚከላከል አንዳችም ጦር በቦታው ሥላልነበረ፣ኦሮሞዎች እያንዳንዱ ወረዳ ውስጥ ኗሪ የነበረውን ሕዝብ እየፈጁ ሰፊ መሬት ያዙ።በእነዚህ ወረዳዎች ውስጥ በአብዛኛው ኗሪ የነበሩት **አማራዎችና ሀዲያዎች** ነበሩ።በግራኝ ጦርነት የደቀቁ ሥለነበር ምንም ዓይነት መከላከል አላደረጉም።

**በ1538ዓ.ም ባሊ(ባሌ) ሙሉ በሙሉ ተወርሮ አብቅቶ፣የኦሮሞ ጦር ደዋሮ(ሐረር)ና ፈጠጋር(አርሲ) ሠፈረ። የከረዩ ነገድ በአብዛኛው ከወላቡ ተንቀሳቅሶ በሥሩ ያሉት በሜልባ ገዳ አስተዳደር የተመራው የጃዊ እና በሙደና ገዳ አስተዳደር የተመራው የባርቱማ ጎሣዎች ወግተው በያዙት በባሊ(ባሌ) ላይ ሠፈሩ።**

**በ1543**ዓ.ም ደዋሮ(ሐረር) ድንበር ላይ የሰፈረው የኦሮሞ ጦር ወደፊት በመግፋት ከፊል ፈጠጋርን(አርሲን) ሲወር ሠለባ የሆኑት **የአገሩ ነባር ነዋሪዎች የሀድያ፣የከንባታና የአማራ ሕዝብ ነው**።

አፄ ገላውዲዎስ ፈጠጋር(አርሲ) ውስጥ የመደበው "ቆለታ" የተባለው ጦር በከረዩ ነገድ ጦር ወደመ።እንደገና "አዳል መብረቅ" የተባለውን የተጠናከረ ጦር ቢልከም አዳል መብረቅም ተሸነፈ።አፄ ገላውዲዎስ ከዚህ በኋላ ነው ዳግመኛ ከግራኝ ቀጥሎ ጠንካራ ወራሪ እንደመጣበት የተረዳው።ንጉሡ አፄ ገላውዲዎስ የራሱን ጦር እየመራ "አሣ ዘነብ" ከተባለ ቦታ ከከረዩዎች ጋር ተዋግቶ አሸነፋቸው።ብዙ የኦሮሞ ሠራዊትም አለቀ።ይሁን እንጅ አፄ ገላውዲዎስ ግራኝ ያፈረሳቸውን አብያተ ክርስቲያናት ለማሠራት ወደሰሜን ተቻኩሎ ሥለተመለሰ የተሸነፉት ኦሮሞዎች ብዙም ወደኋላ ሳይመለሱ በነበሩበት ቆሙ።በዚህ ዘመን የነበረው የኦሮሞዎች አሥተዳደር የኪሎሌ ገዳ ነበር።የደዋሮ ጦርነት ሲደረግ ቱለማ፣ሜጫና ወሎ የተባሉት ታላላቅ ነገዶች ገና ከወላቡና ከኡዳ ነቤ አልተንቀሳቀሱም።ሆኖም ሥንቅና ፈረስ ለቀደሙት የከረዩ ጦረኞች ያቀብሉ ነበር።

**በ1551**ዓ.ም በሚችሌ ገዳ የሚመራው ጦር የቀሩትን የደዋሮንና የፈጠጋርን ወረዳዎች ለመውረር እንደገና ተንቀሳቀሰ።የንጉሱ የአፄ ገላውዲዎስ ጦርና የሚያ ቀሥተኞች ከኦሮሞዎች ጋር "ደጎ"ከሚባል ቦታ ላይ ተዋግተው ኦሮሞዎች አሸነፉ።የሚያዎችን መርዘኛ ቀስት የሚከላከል ከበሬ ቆዳ የተሠራ ጋሻ ኦሮሞዎች አዘጋጅተው ሥለነበር የሚያ ቀስተኞች የተጠበቀውን ውጤት አላስገኙም።በዚህ ጦርነት ደዋሮና ፈጠጋር ሙሉ በሙሉ በከረዩ ኦሮሞዎች እጅ ወደቁ።ሥለዚህ ጦርነት በጊዜው የነበሩት አባ ባሕርይ የተባሉ መነኩሴ ስለኦሮሞ ጦረኞች የጭካኔ ግድያ በግዕዝ በፃፉት ማስታወሻቸው "ከበግና ከፍዬል በቀር

ሰውን ወንዱንም ሴቱንም ከብቱንም ገደሉ" ብለዋል።ቤርሙዴዝም በተወው ማስታወሻው ላይ ሥለጦርነቱ የጭካኔ አገዳደል ተመሳሳይ ቃል ትቶልናል።

***መጋቢት 27ቀን*** 1551ዓ.ም ገዋኔ ወንዝ አጠገብ ሀዘሎ ከተባለ ቦታ አፄ ገላውዲዎስ እና ተጠናክሮ የመጣ የግራኝ ዘመድ ዐሊ ኑር ታላቅ ጦርነት አድርገው አፄ ገላውዲዎስ በጦርነቱ ተሸንፈው ሞቱ። ማንም ቢያሸንፍ አሸናፊው ጦር የተዳከመ ስለሚሆን ኦሮሞዎች ሊገጥሙ አድፍጠው ይጠብቁ ነበር።

የዐሊ ኑር ሰዎች በድል ሰክረው ወደሐረር ሲመለሱ ዐሊ ኑርና ጥቂት ሰዎች ሲተርፉ፣ ብዙዎቹ ባላሰቡት ቦታና ጊዜ በኦሮሞ ጦር ረገፉ።ከረዩዎችም ጦሩን ተከታትለው ሐረርን ወጉ።ሕዝቡንም ወጉ።ለምና ደጋውን የሐረር አውራጃዎች ሠፈሩበት። **የሠፈሩባቸውን ወረዳዎችና አውራጃዎች ሥም የጎሳዎቻቸውንና የሰዎቻቸውን ስም ሰጡ(አቦራ-ወበራ አውራጃ፣ጨርጨር፣ድሬዳዋ፣ጋራ ሙለታ፣ጉርሱም ወዘተ)**። እነዚህ ሁሉ ቦታዎች ከዚህ ወረራ በፊት በሌላ ሥሞች ይታወቁ ነበር።ዐሊ ኑርም ሐረር ከተማን ከኦሮሞ ጦረኞች ለመከላከል ሲል በሐረር ከተማ ዙሪያ እሥከዛሬ የሚታየውን አጥር አሣጠረ።ከረዩዎችን ግን አላቆማቸውም።

ከላይ እንደተገለፀው እሥካሁን ያለውን ወረራ ያካሄደው የከረዩ ነገድ ነበር።ቀሪዎቹ ሦሥቱ ነገዶች ወላቡና ኦዳ ነቤ እየጠበባቸው ሥለሄደ እርስ በርሳቸው በማይጣሉበት ሁኔታ የሚወሩትን አካባቢ በዕጣ ለመከፋፈል ተስማሙ።

ከረዩዎች የወረሩትን ባሌን፣ደዋሮን፣ፈጠጋርን እንደያዙ እንዲቆዩ ሥምምነት ተደርጎ ለቀሪዎቹ ሦሥቱ ነገዶች በወጣው ዕጣ መሠረት፣

1ኛ)ከአዋሽ በስተምዕራብና በስተደቡብ የሚገኘውን አገር <u>**የመጫ ነገድ**</u> እንዲወር፣

2ኛ)በስተሰሜን ምሥራቅ ያለውን አገር <u>**የወሎ ነገድ**</u> እንዲወር፣

3ኛ) ከአዋሽ ወንዝ በስተሰሜን ያለውን <u>**የቱለማ ነገድ**</u> እንዲወር ወሰኑ።

በተደረገው ክፍፍል መሠረት እያንዳንዱ ነገድ ያደረገውን ጉዞና ነባር የኢትዮጵያ ሕዝብ እያሥለቀቀ የያዛቸውን ግዛቶች እንመልከት።

## <u>የመጫ ነገድ ጉዞ</u>

መጫዎች ጉዟቸውን ከመጀመራቸው በፊት አዋሽ ወንዝ ላይ ከቱለማ ነገድ ጋር ብዙ ከብቶች አርደው በልተው ጠጥተው ተላቅሰው ተለያዩ።መጫዎች ከወረራው በፊት ፈረሰኛ ሰላዮችን አሥቀድመው እየላኩ የሚሰፍሩበትን ቦታ አዘጋጁ።ጊቤ ወንዝ አካባቢ "ጡጤ

ብስል"ከምትባል ጉብታ ሥፍራ ላይ ሠፈሩ።ለከብቶቻቸው ሣርና ውሃ እንደልብ የሚገኝባት አካባቢ ነበረች።ከዚች ሥፍራ በመነሳት የመጫ ፈረሰኞች የጋፋቶችንና የእናርያዎችን አገር ዳሞትን እና ቢዛምን ወጉ።የእናርያ ነገዶች ብርቱ መከላከል ቢያደርጉም ሥለተሸነፉ ብዙዎቹ ዐባይን ተሻግረው ዛሬ ጎጃም ክፍለ ሀገር ውስጥ ከሚገኘው ዳሞት አውራጃ ውስጥ ተሰደው ሠፈሩ።በዚያን ጊዜ <u>ዳሞት</u> ከጊቤ ወንዝ አንሥቶ የዛሬውን <u>ጎጃምን</u> የሚያጠቃልል ሠፊ ግዛት ነበር።<u>ቢዛም</u> ደግሞ መጫዎች ከሠፈሩበት በኋላ <u>ወሊጋ</u> ብለው የቀየሩት ክፍለ ሀገር ነው።ዳሞትና ቢዛም ለንጉሱ የሚገብሩ በዛሬው አጠራር ክፍላተ ሀገራት ነበሩ።ጡጤ ብስል በሰውና በከብት ብዛት በመጥበቧ በመጫዎች መካከል ጠብ ተጀመረ።ጠቡን ለመፍታት ግዛት ማስፋፋት ነበረባቸው።ባደረጉት ስምምነት መሠረት በመጫ ነገድ ሥር የተሰባሰቡት ጎሣዎች የሚከተለውን የአገር ክፍፍል አደረጉ።

(ሀ) የጨሊያና የሊበን ጎሣዎች ከጡጤ ብሥል እስከ ግንደ በረት ያለውን ያዙ፣

(ለ)ሌቃ የተባለው ጎሳ ከጊቤ ቱሉ ወለል ብለው እስከሰየሙት ተራራ ድረስ ያለውን ለምና ሀብታም አገር ያዘ።ይህም ቢዛምንና በከፊል ከፋን(ከፋ ጥንትም ስሙ ከፋ ነበር) እና "ላሎ ቅሌን"(በኋላ ኢሉ አባ ቦር ቀጥሎም ኢሉባቡር የተባለውን)አካባቢ ያጠቃልላል።ሌቃዎች ቱሉ ወለልን የጭዳ ማረጃና የአምልኮ ቦታቸው አደረጉ።ሥለ ቱሉ ወለል ግጥምና ዘፈኖችም አወጡ።ከፋና ላሎ ቅሌ ውስጥ የያዙት መሬትም በአብዛኛው የነባሮቹ የአንፊሎዎች ነው። አንፊሎዎች ብዙ ቢከላከሉም ሥለተሸነፉ ሌቃዎች "ገባሮ" የሚል ሥም ሠጥተዋቸው አብረው ኖረው ተዋህደዋል።የአንፊሎዎች ቋንቋ እየሟሸሸ ቢሆንም ከቄለም በስተምዕራብ በሚገኙ አካባቢዎች እሥከዛሬ ይነገራል።

(ሐ) ሁሌ የተባለው ጎሳ ደግሞ ከዴዴሳ ወንዝ እሥከጎጀብ ወንዝ ያለውን፣

(መ) ጂማጉማ፣ጌራና ሊሙ የተባሉት ጎሣዎች ተሰባስበው የጊቤን መንግሥት አቋቋሙ። ይህም የእነጅማ አባጅፋር አገር መንግሥት መሆኑ ነው።

ከቄለም በሥተም ዕራብ ያለው አካባቢ የበረሀ ወባ ያለበት በመሆኑ ለመጫዎች አመች ቦታ አልሆነላቸውም።ሥለዚህ የአካባቢው ነባር ሕዝብ <u>ጋምቤላዎች</u> ከወረራ ተረፉ።

## <u>የወሎ ነገድ ጉዞ</u>

የወሎ ነገድ ከዝቋላ እሥከይፋት ድረስ ከሜያዎች ጋር እየተዋጋ በሥተምዕራብ አድርጎ ወደሰሜን በመጓዝ እንደገና ወደግራ ተቀልብሶ አንጎት(ራያ) የተባለውን አማርኛና የአማራ ባሕል የዳበረባትን የጥንት የአማራ አገር ወረረ።አንጎት ከመድረሳቸው አስቀድሞ "ጊዮርጊስ ኃይሌ" የተሰኘ የንጉሡ ጦር ገጥሟቸው አሸንፈውት ተጓዙ።የተጓዙትም በአዳልና በአማራ መካከል ሲሆን የግራኝ ጦር ለዘመናት ያዳከመው በመሆኑ ከባድ ጦርነት አልገጠማቸውም።

ወደሰሜን በማቅናት የአንጎት አካባቢንና ዛሬ የጁ(ቤተ አማራ)፣ራያና አዘቦ ተብለው የሚታወቁትን አካባቢዎች ቀጥሎም ጋንዘንንና ሳይንትን ወረው ሰፈሩባት።የሰፈሩባቸውንም ቦታዎች እንደተለመደው የመሪዎቻቸውን በአጠቃላይ የጎሳዎቻቸውን  እና የጥንት ቦታዎቻቸውን ሥም ሰጡ።ለምሳሌ የጥንት ሥሙ ላኮ መልዛ የነበረውን በጎሳቸው  ሥም ወሎ አሉት፣ዋስልን ወረሂመኖ አሉት፣መጀመሪያ ኢትዮጵያ ሲገቡ በነበሩበት አካባቢ በሚገኘው "ገላን"ወንዝ ሥም "ገላና"የሚባል ወንዝ የጁ ውስጥ ሰይመዋል።መቻሬ፣ ጉባላፍቶ፣መርሳ፣ውርጌሳ፣ወረኢሉ፣ወረባቦ፣ ወሎ ቦረና ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው።

ከሳይንት ወረራውን በመቀጠል ባርቱማ የተባለው የወሎ ነገድ አማሮች የሚኖሩበትን በጌምድርን ለመውረር ሞክሮ ብርቱ ጥቃት ሥለደረሰበት ወደኋላ ተመለሰ።

በመጨረሻም ዛሬ አማራው በብዛት በሚኖርባቸው ቦታዎች፣ጋሎች(ኦሮሞዎች) በአማራው ከበባ ተደርጎባቸው፣የሸሸው ሸሽ፣ቀሪዎቹ ባሉበት በመቅረት ከአማራው ከአገውና ከሌሎችም ጋር እየተጋቡ ዛሬ ድረስ ዘልቀዋል።

## <u>የቱለማ ነገድ ጉዞ</u>

ሦሥቱ ነገዶች ወረራዎችን ሲያከናውኑ የቱለማ ነገድች በዕጣ የደረሰውን አካባቢ ለመውረር ከኦዳ ነቤ አልተነሳም ነበር።

**በ1562**ዓ.ም ከአዋሽ በስተሰሜን ያለውን ሸዋን ለመውረር ተንቀሳቀሱ።በወቅቱ የነበረው ንጉሥ አፄ ሚናስ አዝማች ዘረ ዮሐንስ የተባለ ሠው የሚመራውን ጦር ቢልክም፣ቱለማዎች አዝማቹንም ገደሉ፣ጦሩንም በታተኑት።ወደፊት በመግፋት ዛሬ የሸዋ ኦሮሞ ያለበትን ምድር ሠፈሩበት።

ሸዋ የመንግሥት እምብርት የነበረች በመሆኗ ከሌሎች አካባቢዎች መወረር የበለጠ መንግሥትን አሳስቦታል።ይሁን እንጅ የአፄ ሚናስ መንግሥት ከአፄ ገላውዲዎስ ዘመን የባሰ የተዳከመ መንግሥት ሥለነበር ወረራውን ለመከላከል ያደረገው ሙከራ ሁሉ ፍሬ አልባ ነበር።

**የአማራ ሕዝብ ለም ከሆነው አገሩ ከባሊ(ባሌ)፣ከደዋሮ(ሐረር)፣ከፈጠጋር(አርሲ፣ሲዳሞና ጎምጎፋ) እና ከመሃል ሸዋ በወረራው ተፈናቅሎ ወደሰሜን ሸዋ ተሰደደ።**

አፄ ሚናስ ሞቶ አፄ ሠርፀ ድንግል ሥልጣን ሲይዝ ወረራውን ሊያቆም ባይችልም ከሁሉም ነገሥታት የበለጠ ተዋግቶ ብዙ ድሎችን በወራሪዎች ላይ ተጎናፅፏል።

**በ1567**ዓ.ም የሠርፀ ድንግል ጦር ዝዋይ ሐይቅ አጠገብ ደርሶ በአካባቢው የሰፈሩትን "የአባቲ"ጎሳዎችን ወግቶ አሸነፋቸው።በአባ ባሕርይ ማስታወሻም መሠረት በዚህ ጦርነት ከ10ሰው በላይ አላመለጠም።

*ሥርፀ ድንግል ዝዋይ ላይ ድል ቢያገኝም በዚሁ ወቅት ሸዋና ጎጃም ድንበር ላይ የሠፈሩ ቱለማዎች ተጠናክረው ዐባይን ተሻግረው ጎጃምን ወረሩ።ሠርፀ ድንግልም ወረራውን ለመቋቋም "አደራ" ከሚባል ቦታ ከቱለማውች ጋር ተዋግቶ አሸነፋቸው።በዚያው ወቅት ዋግ መወረሩን ሰምቶ ይህንኑ ወረራ ለመከላከል ወደዋግ ሲሄድ በምዕራብ በኩል የነበሩት መጫዎች ዳሞትን ወርረው ዘረፉ።በአማራዎችና በጋፋቶችም ላይ ብዙ እልቂት አደረሱ። በሥተምሥራቅ ደግሞ ቱለማዎች ሸዋን እንደገና ወርረው ተጠናክረው ሠፈሩበት።ወረራውን የማቆሙ ጦርነት ለንጉሱ የህልም ሩጫ ሆነበት።ወራሪዎቹ አዲስ የሠፈራ ምድር ለማግኘት የጀመሩት ጦርነት የተሳካ ሆነ።ቀደም ሲል እንደተገለፀው ጋሎች(ኦሮሞዎች) ከበርበራና ከቤናድር በርሃዎች በሶማሌና በባንቱ ጦረኞች ተባርረው ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ መጥተው የሠፈሩበት ዘመን በታሪክ ሂደት ውስጥ በጣም ቅርብ ጊዜ ነው።ከወላቡና ከኦዳነቤ ተነስተው የኢትዮጵያን አብዛኛውን ግዛት በወረራ ሲይዙ የፈጀባቸው ጊዜ ከ60ዓመት አይበልጥም።የግራኝ ወረራ ዓላማ የእስልምናን ሃይማኖት ለማስፋፋትና ግዛት ለማግኘት ሲሆን፣ የጋሎች(የኦሮሞዎች)ወረራ ዓላማ ግዛት(የመሥፈሪያ መሬት) ለማግኘት ነበር።*

**ከ1517-1567ዓ.ም በነበረው ዘመን ኢትዮጵያ ከአንድ አሥከፊ ወረራ ወደሌላ አስከፊ ወረራ ተሸጋገረች።ግራኝ የቀደደው የወረራ በር ጋሎችን(ኦሮሞዎችን) አሥገባ።**

*ምንም እንኳን ኦሮሞው በአማራው ላይ መጠነ ሰፊ ጭፍጨፋና ግድያ መፈፀሙ ባይካድም፣ በአጠቃላይ በኦሮሞ ወረራ ሂደት ሠለባ የሆኑ ነገዶች ቁጥር ሥፍር የላቸውም። ሀዲያዎችና ከምባታዎች ከመኖሪያቸው ከባሌና ከአሩሲ ተፈናቅለው በደቡብ ምዕራብ ሸዋ በሥደተኝነት አነስተኛ ቦታ ይዘው እንዲኖሩ ተደርገዋል ። በዝዋይ ሐይቅ ደሴት አካባቢ ተወስነው የኖሩት በቀሥት የታወቁት የሜያ ነገድም በግራኝም ሆነ በኦሮሞ ወረራ ጦርነት ተመናምነው የት እንደደረሱ አይታወቅም። የጋፋት ነገድም ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል። አርጎባዎች፣ቀቤናዎች፣ወርጅዎች፣ላላባዎች፣ሲዳማዎች የኦሮሞ ወረራ ሰለባ ሆነዋል። የዳውሮና የገሙ ሰዎች ግዛታቸው በኦሮሞዎች ተወስዶባቸዋል።ከየትኛውም ነገድ፣ ከግድያው የተረፉት በጋላ(በኦሮሞ) የሞጋሣ ሥርዓት*

*የማድረግ ሥርዓት ነው)ሳይወዱ በግድ ኦሮሞ እንዲሆኑ ወይም እንዲሰደዱ ሆነዋል።*

*ይህ ተግባር ዛሬም በጃራ የተመራው የኦሮሞ እስላማዊ ድርጅትም የአማራ ሴቶችን አሥገድዶ ኦሮሞ በማድረግና በማስለም እስከማግባት ዘልቋል።*

አባቶቻቸው በጋላ(ኦሮሞ)ወረራ የተገደሉባቸውን የሌሎች ነገዶችን ልጆች ጋሎች(ኦሮሞዎች) በጉዲፍቻ ሥራዓት ውስጥ በማዋል አገልጋይና ከብት ጠባቂዎች ያደርጓቸው ነበር።

በአጠቃላይ ጋሎች(ኦሮሞዎች) ይህንን መጠነ ሠፊ ወረራ ባካሄዱባቸው አካባቢዎች ውስጥ የነበሩትን ነገዶች፣ለጀግንነታቸው መለኪያ ይሆን ዘንድ የወንዶችን ብልት በመሥለብ ሳይገቱ ነገዱንም የራሳቸው ለማድረግ "የሞጋሳና የጉዲፍቻ"ሥልቶችን ተጠቅመዋል።ይህ ብቻ አይደለም።

**በግራኝ ወረራ ክፉኛ የተጎዳው የአማራና የክርስቲያን ዕምነት ተከታይ ሕዝብ ጥንት ይኖርባቸው የነበሩትን ባሊን(ባሌን)፣ፈጠጋርን(አርሲን፣ሲዳሞንና ጎምጎፋን)፣ ደዋሮን(ሐረርን)፣ቢዛምን(ቄለም ምዕራብ ወለጋን)፣ዳሞትን(ሌቃ ምሥራቅ ወለጋን)፣ እናርያን፣ወዘተ፣በአጠቃላይ ድንግልና ለም መሬቶች በግዳጅ በቀላሉ እንዲለቅ አሥገደዱት።የነባሩን ሕዝብ ሀይማኖት፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ግንኙነትን አሥለወጡ።**

የጋሎች(የኦሮሞዎች) ወረራ ካበቃ በኋላ የሕዝብ ውህደት ተጀመረ።ለመዋሀድ የወሰደው ጊዜም አጭር ነበር።አብሮ በመኖር የባህልና የቋንቋ መወራረስ ተደረገ።በአቴቴ(ጨሌ) ማምለክ፣ቦረንቲቻ ማረድ፣አድባር ሥር ቡና ማፍላት፣ጭዳ ማረድ ወዘተ ከገዳ ሥርዐት አምልኮ የተወሰደ ነው።ጋሎች(ኦሮሞዎች) በወረራ ከመጡ በኋላ ከነባሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አብረው በመኖር ረጅም የሰላምና የመረዳዳት ዘመን አሳልፈዋል።

**ከ17ኛው(ከአሥራ ሰባተኛው) ክፍለ ዘመን ጀምሮ ያለው የኢትዮጵያ ታሪክ የኦሮሞ ሕዝብ ጭምር የሠራው ነው።**

## <u>ክፍል4</u> <u>የኦነግ የግዛት ጥያቄና የኢትዮጵያ አንድነት</u>

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር(ኦነግ) በመባል የሚታወቀው ጠባብ ጎሰኛ ድርጅት ኦሮሞዎች የሚኖሩበት አካባቢ ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ ራሱን የቻለ አገር እንዲመሠረትና ኦሮሞ ያልሆኑ ነዋሪዎች ከአካባቢው እንዲወጡ በማለት በተለያየ መንገድ በተለይም በአማራ ሕዝብ ላይ ግድያ፣ማፈናቀልና ዝርፊያ ፈፅሟል።ለኦሮሚያ መንግሥት እውን መሆን እንዲረዳ የሀሰት ታሪኮችን ኦነግ እየፃፈ ነው።የኢትዮጵያ ታሪክ የ100ዓመት ነው ከሚለው ጀምሮ ሌሎቹን ታሪኮችም እንመልከት። (1) አማሮች የኦሮሞዎችን አገር በጉልበት መጥተው ያዙ፣(2) አማሮች የኦሮሞዎች መተዳደሪያ የነበረውን የገዳ ሥርዓት አጠፉ በማለት ይኮንናሉ።

የእነዚህን ነጥቦች ይዘት በየተራ እንመርምር፣

(1) አማሮችና ሌሎች የኢትዮጵያ ዜጎች የትኛውም ክፍለ ሀገር አገራቸው እንደሆነ ያምናሉ። በዚህም ዕምነት መሠረት በየቦታው ሄደው ይኖራሉ።ሆኖም ኦነግ የግዛት ባለቤትነት ጥያቄ ስላነሳ ታሪካዊ መሠረቱን ማሳዬት አለብን። ኦነግ ኦሮሚያ ብሎ የሚጠራው አካባቢ ዓለም ሥትፈጠር ጀምሮ ኦሮሞዎች የነበሩበት አሥመስሎ ይነግረናል።የኦነግ የሶሺዎ፣ኢኮኖሚክና የፖለቲካ አመለካከት የሕዝብን ከቦታ ወደቦታ ዝውውር ከግምት ውስጥ አያስገባም።ሁሉም ነገር የህዝብ ዝውውርን ጨምሮ የማይነቃነቅ ቀጥ ብሎ የቆመ ነው።ዕውነቱ ግን ሠዎች እንኳን በአንድ አገር ውስጥ በአንድ አህጉር ይዘዋወራሉ፣ይሰፍራሉ፣ይኖራሉ።ትውልድም ትተው ያልፋሉ።ለምሳሌ የአሜሪካ፣የካናዳ፣አብዛኛውየአወስትራሊያና የኒውዚላንድ ወዘተ ሕዝብ የትውልድ ሀረጉ የሚመዘዘው ከሌላ አህጉር ነው።በየግል ካየነው ከኢትዮጵያ የመጣን ቢሆንም የምንኖርባቸው የአውሮፓም ሆነ የአሜሪካ ወዘተ አህጉር የእኛም መኖሪያ ሆነዋል።ለሌንጮ ለታም፣ለሌንጮ ባቲም፣ለአሰፋ ጀለታም፣ለቡልቻ ደመቅሳም፣ ለዲማ ነገዎም፣ለአባ ጫላ ለታም፣ለዳውድ ኢብሳም፣የዛሬው የኦነግ አቦ ቦሩ በረካም በያሉበት እንዲሁ።

ምንጊዜም እነሌንጮ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚያሥጠይቃቸውን ወንጀል ፈፅመዋል።ምንም ዓይነት ሌላ መኖሪያ የሌላቸውን ድሃ የአማራ ገበሬዎች በዘር አማራ በመሆናቸው ብቻ በሐረር፣በአሩሲ፣በባሌ፣በኤሉባቦር፣በወለጋ፣በከፋ ወዘተ ጭካኔ በተሞላበት ተግባር ከነነፍሳቸው በገደል ተወርውረዋል፣ከነነፍሳቸው ተቃጥለዋል፣ ተገድለዋል።"በኋላ የመጣ አይን አወጣ"እንዲሉ ሆኖ ከመኖሪያ አገራቸው ተፈናቅለዋል፣ የቀሩትም አገራችሁ አይደለም መጤዎች ናችሁ ተብለው ተባርረዋል።

ሥለባላገርነት መብት ስንነጋገር ግልፅ መሆን ያለበት ጥያቄ አለ።ሠዎች ለሚኖሩበት አገር ባለቤት የሚያደርጋቸው ምንድነው? ከሌሎች ቀድሞ መገኘት ከሆነ ኦሮሞዎች ከቤናድር ከመነሳታቸውና ወላቡ(ኢትዮጵያ ውስጥ) ከመግባታቸው በፊት ዛሬ በወረራ የሠፈሩባቸው ቦታዎች(ሐረር፣ባሌ፣አሩሲ፣ሲዳሞ፣ወለጋ፣ወሎ፣ወዘተ)በአማሮችና በሌሎች ነባር ሕዝብ የተያዘ ምድር ነበር።ሥለዚህ ኦሮሞዎች ዘግይተው በ16ኛው ክፍለ ዘመን የደረሱ ሥለሆነ እንደነባር ሕዝብ የባለ አገርነት መብት ላይኖራቸው ነው። ይህ ደግሞ የኦሮሞን ኢትዮጵያዊነት ሊያሥከደን ነው። በሌላ በኩል ተቀባይነት ባገኘው በዓለም አቀፍ የዜግነት ህግ መሠረት የሚኖሩበት ወይም የተወለዱበት አገር አገራቸው ነው ብለን ካመንን ኦሮሞዎች ኑዋሪዎቹን አባርረው ከሠፈሩበት በኋላ የተባረሩት ዜጎች አገር ሠላም ሲሆን መጥተው የሰፈሩበት ኑዋሪዎች የአገሩ ባለቤትነት መብት አላቸው።ሥለዚህ ቀድመውም የኖሩበት ሆነ በኋላ የመጡት የባለአገርነት መብታቸው እኩል ነው።በዚህ መልክ ሥናይ ኦነግ ያነሳው የውጡልኝ ጥያቄ ከጠባብ ጎሰኝነትና ከታሪክ ዕውቀት ድህነት የተነሳ መሆኑ ግልፅ ነው።

(2) የገዳን ሥርዓት በሚመለከት አማሮችም ሆኑ ሌሎች ነገዶች እንዲጠፉም ሆነ እንዲኖር ጥረት አላደረጉም።ሥርዓቱ የጠፋው መጥፋት ሥለነበረበት ብቻ ነው።እንደማንኛውም አሮጌ ባህልና ሥርዓት ጊዜውን ሥለጨረሰ ነው።ኦሮሞዎች በወቅቱ ጦራቸውን እንዲያደራጁ፣አምልኮ እንዲፈፅሙና የተጣላ እንዲያሥታርቁበት የጠቀማቸው ሥርዓት ቢሆንም ለምንገኝበት ዘመን  የተሻሻለ ሕግና የአሥተዳደር ሥርዓት ሲመጣ የገዳ ሥርዓት ቦታ እንደማይኖረው ግልፅ ነው።ፍርድ ቤቶች እያሉ የከባድ ወንጀል ጉዳዮች በገዳ ሽማግሌዎች ሊታዩ አይችሉም።ሠዎች የተቀበሏቸው የክርስትናና የእሥልምና ሀይማኖቶች እያሉ በመናፍስት አያመልኩም።ከፈለጉም ማምለክ ይችላሉ።ይህ የሰዎች ምርጫ ነው። የገዳው የአስተዳደር ሥርዓት ዘመናዊ የፓርላሜንታሪ ዲሞክራሲ ሥርዓትን  ሊተካ አይችልም።ለአገሩም ሕዝብ ፍትህና ዲሞክራሲን የሚያጎናፅፍ አይደለም።ኦነግ የኢትዮጵያን መከፋፈል አጥብቆ ይደግፋል።ኦነግ ለኤርትራም መገንጠል ከወያኔ ትግሬዎች ጋር በመሆን የመጀመሪያው ድጋፍ ሰጭ ከነበሩት ውስጥ ነበር።በኦነግ ትንታኔ መሠረት ኤርትራ የኦሮሞ ሕዝብ ጭምር አይደለችም።የኢትዮጵያ መፈረካከስ የኦሮሚያን መፈጠር ያፋጥነዋል ከሚል ድምዳሜ ላይ ይደርሳል።

ምንም እንኳን ይህንን የኦነግ አቋም ለዘመናት ለተከታተልነው ወገኖች እንግዳ ባይሆንብንም፣ለዘመናት ሥለኦነግ አቋም ሲነገረው ማመን አዳግቶት”ጀሮ ዳባ ልበስ” ብሎ ለተቀመጠው ብዙሀን፣ በ2009ዓ.ም(2016በግሪጎሪያን አቆጣጠር) በኦሮሞዎች  ስብሰባ ለንደን ላይ “ኢትዮጵያ ፈርሳ ኦሮሚያ አገር መመሥረት” እንዳለበት ከእነሊበን ዋቆ አፍ ፈንቅሎ ሲወጣና ተወርውሮ ሲፈነዳ፣ብሎም ሞቅ ባለ የኦሮሞ ልሂቃን ጭብጨባ ሲታጀብ ድንጋጤን  ፈጥሯል።

የኦነግ ትንታኔ ትልቁ ችግር ሕዝብ አብሮ በመኖር የፈጠረውን መሥተጋብር መገንዘብ አለመቻሉ ነው።ከአክሱም ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያውያን በደማቸው የጠበቁትንንና ከኦሮሞዎች መምጣት በኋላ በአንድነት የጠበቁት አገር የአማሮች ወይም የትግሬዎች ብቻ አይደለም። የአገሪቱ የባሕር በር የነበሩት ወደቦች አገልግሎት ሲሰጡ የነበረው ለተወሰኑ ጎሳዎች አልነበረም።በዚህም ኦነግ ለኦሮሞ ሕዝብ ጥቅም የቆመ አለመሆኑን አሥመስክሯል። ኦነግ ግቡን ሊመታ የሚችለው የጎሳ ግጭት በማስነሳት እንደሆነ ከወያኔና ከሻዕቢያ ተምሯል።በማንኛውም የኦነግ ስብሰባዎች ላይ ትናንትም፣ዛሬም የመጀመሪያውና ዋናው የውይይት አጀንዳ አማራ ነው።እንዴት የአማራውን ቅሥም መሥበር እንደሚቻል፣እንዴት የኦሮሞውንና ሌሎቹን ነገዶች በአማራ ላይ ማስነሳት እንደሚቻል ዋናው የውይይት አጀንዳ ነው።መጀመሪያ አማራ ካልተመታ ኦሮሚያን የመፍጠሩ ጉዳይ የሚታሰብ  አይደለም። ይህ ነው ዋናው የኦነግ ሥሌት። ሥለዚህ ለግጭቱ መፋፋም እንቅፋት የሆኑ ሁለት ነገሮች ነበሩ።

1) በአጠቃላይ የገጠሩ ኦሮሞ ሕዝብ ከአማራ ሕዝብ ጋር በማህበራዊ ኑሮና በኢኮኖሚው የተሳሰረ በመሆኑና ሁለቱም ወገኖች ለጥል የማያመች መቻቻል ያለበት ባህል ያላቸው መሆናቸው፣

2) በከተማ ያለው ሕዝብ በአብዛኛው እርስ በርሱ የተጋባና የተዋለደ ከመሆኑም በላይ በአስተሳሰቡ ከዘርና ከሃይማኖት ልዩነት ዕምነት የተላቀቀ መሆኑ ናቸው።

በ1970ዎቹ መጨረሻ ላይ ኦነግ በደረሰበት ውሳኔ መሠረት ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ቢኖሩም ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ከጊዜ ብዛት ሁለቱን ችግሮች አስወግዶ የኦሮሞን ሕዝብ በኦነግ ሥር ማሰለፍ እንደሚቻል ታምኖበት ለዚሁ ይረዳ ዘንድ የሚከተሉት መፈክሮች በተራ አባላት በሰፊው እንዲነገርና እንዲሰራጭ ተደረገ።

**-ያ ጀሩ ጀረሪቲ ያ ጀሩ ጀረሪቲ፣አማርቲቲን ነማ ሚቲ (አማራ ሰው አይደለም)**

**-አማራን ሃሬ ዳ (አማራ አህያ ነው)**

**-kill the Amharas(አማራን መግደል ነው)**

**-to succeed intensify your hatred over your enemy(ለማሸነፍ ጠላትህን አጥብቀህ ጥላ)**

በቀይ ሽብር የተገደሉ የኦሮሞ ሰዎች እየተመረጡ የአማራ መንግሥት የገደላቸው፣ ለኦሮሚያ ነፃነት የሞቱ ኦሮሞዎች እየተባለ በኦነግ መፅሔቶችና በራሪ ወረቀቶች ላይ ይወጣ ጀመር። ከገዳዮቹ እነቀልቤሳ ነገዎና እነ አሊ ሙሳ እንዳሉበትና ከሟቾቹ አማሮችና ሌሎች ዘሮችም እንዳሉ ግን አይገልፁልንም።ጥል በተባባሰና ደም በፈሰሰ ቁጥር ልዩነት እየሰፋ ይሄዳል፣ብዙ መተላለቅ ይደረጋል።ከዚያ በኋላ አማሮችና ኦሮሞዎች ጠላት ሥለሚሆኑ አብረው ሊኖሩ አይችሉም።ይህም የኦሮሚያን መፈጠር ዕውን ያደርገዋል።

በዚህ ዕምነት መሠረት **ከትግሬ ወያኔዎች ጋር ሥልጣን ላይ ሲወጡ፣ ኦነግ የድርሻውን ሥልጣን ያገኘ ጊዜ የወሰደው እርምጃ በደኖና ወተርን ጨምሮ በምሥራቅና ምዕራብ ሐረርጌ፣አሩሲ፣ባሌ፣ኢሉባቦር፣ወለጋ ውስጥ አማሮችን መግደልና፣መደብደብ፣ማባረር ነበር። በወቅቱ የምክር ቤቱ አባል የነበረው የኦነግ ተወካይ ኃላፊነቱ የኦነግ መሆኑን አመነ። የሚያሥከትለውንም ችግር በማዬት ሌንጮ(ዮሐንስ) ለታ በአሥሸኳይ አሥተባበለ።**

ኦነግ በወያኔ ፊት ተነሥቶት ሲገፈተርና ከሽግግር መንግሥት ተብዬው ሲወጣ በወቅቱ የማሥታወቂያ ሚኒስቴር የነበረው ዲማ ነጎ የሚባለው የኦነግ አባል ሥልጣኑን ከመልቀቁ በፊት በመጨረሻዋ ሰዓት በአረምኛ የራዲዮ ፕሮግራም ያሥተላለፈውን ማጤን አለብን።

”በእጃችሁ ባለው መሣሪያ በጠላታችሁ ላይ ተነሱ” ብሎ ነው ከሥልጣን የተሰናበተው። ግለሰቡ ይህንን መልዕክት በራዲዮ ሲያሥተላልፍ ሰላምን፣አንድነትን፣ነፃነትን፣ዲሞክራሲን መስበኩ አይደለም።እስከዛሬዋ ዕለት ድረስ የኦነግ የመጀመሪያው ጠላት አማራ ሥለሆነ፣ እንደሩዋንዳ ሁቱዎችና ቱትሲዎች ዓይነት እልቂት እንዲጀመር መቀስቀሱ ነበር።ግን ያልተማረው ተራ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮ በመኖር ያለው አስተሳሰብ ከኦነግ ብዙ የላቀ ስለሆነ፣ ኦነግ የሕዝቡን ድጋፍ ባለማግኘቱ የተመኘው ዕልቂት እንዳሰበው አልሆነለትም። ግን ኦነግ እንደድርጅት ያሰበውን ያህል ባይሆንም በዚያች በሥልጣን ላይ በነበረባት አጭር ጊዚያት  ውስጥ ብዙ አማራዎች ጨርሷል።ቀኝም ነፈሰ ግራ የኦነግ ሰዎች የሚደክሙለትን የመሪነት ሥልጣን ለመያዝ እድል አላገኙም።

ሠዎች ኦሮሞ በብዛት ከሚኖርባቸው አካባቢዎች(ኦሮሚያ ተብዬው) ወደመጡበት አገር ይመለሱ የሚለው የኦነግ ፖሊሲ ሥራ ላይ ቢውል ከመጥፎ የሞኝነት ሥራ ውስጥ እንገባለን።ቀድሞ የመጣው ሲኖር በኋላ የመጣው ሊወጣ ነው።እንግዲህ አወጣጡ በኋላ ከመጣው ሲጀመር፣ኢትዮጵያ ውስጥ ሰፍረው የሚኖሩ ኦሮሞዎች በሄዱበት አኳኋን ከየአቅጣጫው ተሰባስበው  በመጀመሪያ ወደ ኦዳ ነቤ፣ከኦዳ ነቤ ወደ ወላቡ መመለስ ሊኖርባቸው ነው። **በዚህ ጊዜ ወሎ ላኮ መልዛ፣የጁ ቤተ አማራ፣ወረኢሉ ዋስል፣፣ወለጋም ቢዛም፣አርሲ፣ሲዳሞና ጎምጎፉም ፈጠጋር፣ሐረር ደዋሮ፣ኢሉባቡር ላሎ ቅሌ**  ወዘተ ይሆናሉ።እነሌንጮ ለታ፣እነዲማ ነጎ፣እነዲማ ጉርሜሳ(ሻምበል ወልደሰንበት) እነቡልቻ ደመቅሳ፣እነአሰፋ ጀለታ፣እነ ሌንጮ ባቲ፣እነቦሩ በረካ ከያሉበት ሄደው በነገሌና በአባያ አካባቢ ወደሚገኘው ወላቡ  ይገናኛሉ።ከዚያም ወደቤናድር አውራጃ ቀጥሎም ወደ በርበራ ይሄዱና ይሠፍራሉ።እዚህ ላይ አንድ የሚነሳ ችግር አለ። ከኦሮሞና ከሌላ ዘር የተወለዱ ሰዎችስ እንዴት ይሆናሉ?ለዚህ ኦነግ አስቀድሞ የወሰነውን መፍትሔ ሥራ ላይ ያውል ይሆናል።ተደጋግሞ እንደሰማነው የትግሬው ወያኔ በትግሉ ወቅት እንቅፋት ናቸው ያላቸውን እንዳረዳቸው ሁሉ፣ለኦነግ ትግል እንቅፋት ናቸው  የሚባሉት እነዚህ ሰዎች መጀመሪያ መታረድ አለባቸው።ይህ ሲሆን ደግሞ ብዙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልቃል።በዚህም ኦነግ እወክላለሁ የሚለውን ሕዝብ አለመወከሉን እናረጋግጣለን።

ይህ የኦነግን የውጡልን ጥያቄ ሠፋ አድርገን ካዬን የበለጠ ከልጆች ጨዋታ የባሰ ከንቱ ሆኖ እናገኘዋለን።ከላይ ባጭሩ ልናሳይ እንደሞከርነው ዛሬ አብዛኛው የዓለም ሕዝብ የሚኖርበት ሥፍራ የመጀመሪያው ትውልድ የኖረበት ሥፍራ ሳይሆን በዝውውር የሰፈረ ነው።

ከሰሜን አሜሪካ ብንጀምር ድፍን አሜሪካና ካናዳ ወደአውሮፓ መጓጓዝ አለበት።ለዚህም ምን ዓይነት መጓጓዣ ይበቃ ይሆን? እነክሊንተን፣እነቡሽና ትራምፐ ከእነቤተሰቦቻቸው መጀመሪያ መሣፈር ሊኖርባቸው ነው። ጥቁር የሰሜን አሜሪካ ሕዝብ ወደአፍሪካ መሄድ አለበት።ነባር ናቸው የሚባሉት ዘሮች ደግሞ ወደ እስያ መሄድ አለባቸው።ኦሮሞ ውሎ

ያደረበት ምድር ሁሉ ኦሮሚያ ይሆናል ካላሉን በስተቀር፣ግሪን ካርድና ዜግነት የወሰዱትም ኦሮሞዎች ወደ ወላቡ ከዚያም ወደቤናድርና ወደበርበራ መቀጠል ይኖርባቸዋል።

በዚህም ገፅታው ሲታይ የአነግ የውጡልን ጥያቄ የፖለቲካ ቂልነት እና የቲዎሪ ድህነት የሞላበት፣በማንኛውም መንገድ የአንድ ጎሳ መንግሥት መሥርቶ ሥልጣን ለመጨበጥ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም።

## <u>ሌንጮ ለታና ማሥረጃዎች</u>

ሌንጮ ለታ በነጮች አቆጣጠር በ2016ዓ.ም መጨረሻ ላይ ስቶክሆልም ከብርሀኑ ጋር በተገኘበት ስብሰባ ላይ አነግ ከወያኔ ጋር በሰራበት ወቅት በተለያዩ ቦታዎች በተለይ **<u>በበደኖና በአርባ ጉጉ ሥለገደላቸው አማሮች</u>** ጥያቄ ሲቀርብለት የሰጠው መልስ (1)**<u>በደኖ</u>** ገዥው ፓርቲ እንጅ እኛ አይደለንም (2)**<u>አርባ ጉጉም</u>** አህዴድ እንጅ እኛ አላስተዳደርንም የሚሉ ናቸው።ዕውነታው ግን ይህ አይደለም። ምንም እንኳን ያ ወንጀል የተፈፀመበት አካባቢ በአካባቢያዊ ክፍፍል መሠረት ለአነግ ቢደርሰውም፣ወያኔና አነግ መጀመሪያ ሥልጣን እንደያዙ በደኖም ሆነ አርባጉጉ ውስጥ ሁለቱም በወንጀሉ ውስጥ እንዳሉበት ከእነማስረጃው ሥለሚቀርብ በጥሞና ለሚከታተል ሰው ግልፅ ይሆናል።

ለማንኛውም በቅድሚያ ሌንጮ ሥለበደኖም ሆነ ሥለአርባ ጉጉ ቃል በቃል የተናገረው ይኸውና።ቀጥሎም ማሥረጃዎች ይሠፍራሉ፣ፍርዱን ግን ለአንባቢ እተዋለን።

## <u>ሌንጮ ለታ!</u>

-"አነግ ፈፀመ ተብሎ ክስ የሚቀርብባቸው ቦታዎችና ሁኔታዎች ላይ ነው የተነሳው ጥያቄው፣ ይኸ 20ዓመት በላይ ሲያነታርከን የቆዬ ጉዳይ ነው።ምንጩ ምንድነው ብለን እንጠይቅ፣ከዬት ነው የመጣው፣ይህ አብዛኛው ወንጀል የተሰነዘረው አሁን ሥልጣን ላይ ባለው ፓርቲ ነው።በተለይ **<u>በደኖ</u>** የመጀመሪያዋ የመንደርና የወረዳ ምርጫ ሁለት ሳምንት ሲቀረው የመጣ ጉዳይ ነው።በቴሌቪዥን ላይ ለፕሮፓጋንዳ የቀረበ ጉዳይ ነው።ምክንያቱም ግልፅ ነው።ኦሮሞንና አጎራባች ብሔሮችን ፣በኦሮሞ መካከል ሰፍረው ያሉትን ብሔረሰቦች ለማጋጨት ነው።20ዓመት ከዚያ በኋላ <u>ይህንን ማጣራት እንፈልጋለን ካልን የትኛው አጥኚ ቡድን ነው ይህንን ሄዶ አጣርቶ ትክክለኛ ፍርድ ሊሰጠን የሚችለው?</u> መደጋገሙ ግን ማንን ነው የሚጠቅመው?ያን ነው መጠየቅ ያለብን፣ኦሮሞና ሌሎች ብሔሮች እንዲቀራረቡ ያደርጋል ይህን መደጋገሙ? እንተው" አለ።

<u>-"**አርባ ጉጉ**</u> ተፈጠረ የተባለው አነግ አርባጉጉ አያሥተዳድርም ነበር፣ያስተዳድር የነበረው አሁንም ሥልጣን ላይ ያለው የኦሮሞ ቡድን ነው።አነግ በነበርን ጊዜ ማንኛውንም ብሔር

እንደጠላት ፈርጀን ለጥቃት ግልፅ እንዲሆን አድርገን አናውቅም (ተሰብሳቢው ሞቅ ያለ ጭብጨባውን አቀለጠው) ይህን የሚያደርጉትንም ኃይሎች እንቃዎም ነበር።ይህ ዓይነት ቴንዴንሲ (ዝንባሌ ማለቱ ይመስለኛል) ያላቸውንም እንቃዎም ነበር።ብዙ ማለት ይቻላል፣ ግን ኢትዮጵያ አካባቢ የሰው ደም በቀላሉ ይፈሳል። በ97 ምርጫ አዲስ አበባ መንግሥት ራሱ ያቋቋመው አጥ'ፒ ቡድን ከ200 በላይ ነው የሞቱት።ግልፅ ማን ተጠያቂ እንደሆነ የሚታወቀው” አለ።

## ማሥረጃዎች!

**(1ኛ) አባ ኒቆዲሞስ አሰፋ** የተባሉት አባት በኢሳት የሰጡት ምሥክርነት ይኸውና፣

*__“በ1983ዓ.ም__ ገዥው መንግሥት ሥልጣን ተቆጣጠረ።**ኦነግም** መጀመሪያ ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌን እንደተቆጣጠረ፣የመጀመሪያ ሥራ ያደረገው በአማራ ተወላጆች እጅ የነበረን የመሣሪያ ትጥቅ ማስፈታት ነበር።ትጥቅ ፈተው መሳሪያ አሥረከቡ።አሁን ከኦነግ ጋር ተስማምተው መኖር ጀመሩ።*

*ነገር ግን እነጎች ተሥማምተው ሠላማዊ መስለው ቢኖሩም፣ሀብት ያለውን ለትግል ይፈለጋልና ገንዘብ አምጣ ከማለት አንስቶ ሕዝቡ የሰጣቸውን መሳሪያ አምነው ከተቀበሉ በኋላ እንደገና ተጨማሪ መሳሪያ ቀብረሀልና አውጣ እያሉ ይገርፉና ያሰቃዩ ሥለነበር፣ በቀን ህወሀት የተወሰኑ ወታደሮች በመኪና ጭኖ መጥቶ እኔ ነኝ የማስተዳድራችሁ ብሎ ሲመጣ (ሕዝብ ዕውነተኛ መንግሥት መጣልን ብሎ ሁሉም እልልታውን ያሰማል) ተመልሶ ሐረር ከተማ ገብቶ ያድራል። ማታ ደግሞ __**ኦነግ** መጥቶ ምን አይታችሁ ነው እልል ያላችሁት በሚል እርጉዝ እናት ሆዷ ተቀዶ ልጇ ከፊቷ ሲወድቅ በዓይኗ እንድታይ አደረገ፣ሕዝብ እንደጎመን የተቀረደደበትና ወደገደል የተጣለበት ሁኔታ ነው የተፈጠረው። በዚህ ዓይነት **የበደኖ እልቂት** ተፈፀመ__።ከዚህ ከበደኖ ዕልቂት በኋላ ዘጠኝ(9) የአንጫር ወረዳ ቀበሌዎች ምዕራብ ሐረርጌና አሰኮ ወረዳ **አርባ ጉጉ** አውራጃ የነበሩ አማሮች፣ትጥቅ ከፈታን እንደበደኖ ወገኖቻችን ሥለምናልቅ፣ ትክክለኛው መንግሥት እስከሚመጣ ትጥቅ አንፈታም አሉ።ይህን ተከትሎ ኦነግ ለነፍጠኞች ሥንቅና ትጥቅ ታቀብላላችሁ በሚል (1ኛ) ዘጠኝ ሰዎች አቶ በለው ወርቅነህን ጨምሮ በአውሰይድ ወንዝ አርዶ ጣለ፣ (2ኛ) በዳሮ አቦና አካባቢ ከሚጨታ ከተማ አለፍ ብሎ ከምትገኝ ቀበሌ __**አርባ ጉጉ**__ የአቶ ጌታቸውን አሥራ አንድ ቤተሰብ ገደለ፣(3ኛ) ወፌ ከተማ ራብሸዲ ቀበሌ ላይ ልጆች የነበሯቸው ሰባት ወንድማማቾችም እንዲሁ። (4ኛ)የአቶ አቻምየለህ አሰፋ አባት አቶ አሰፋ በኦነግ ኃይሎች ቆዳቸው ተገፎ እንደስልቻ የወጣበትና ተሰቃይተው የሞቱበት ሁኔታ ነበር። በአሰቦት ገዳምም 17አባቶች አልቀዋል። የእነኦነግ ታሪክ የማይረሳ ነው።*

በዚህ ወቅት የአገር ሽማግሌዎች ተሰባስበው ለታምራት ላይኔ አቤቱታ ሲያቀርቡ ያገኙት መልስ፣ "ይኸን ነፍጠኛውን ነው የምትሉኝ? ሐረር ብሎ አማራ፣ባሌ ብሎ አማራ፣አርሲ ብሎ አማራ አላውቅም" ነው ያሏቸው። ከዚህ በኋላ አቅምና ትንሽ ሀብት ያለው ሕዝብ "ለካ ይህ አገራችን አይደለም፣ወደወገኖቻችን እንሂድ በሚል ተነስተው ሄዱ" አሉ።

ከእነዚህ ወሰንተኛ ከሆኑት **ከአንጫር ወረዳ ምዕራብ ሐረርጌ** እና ከአሰቦ ወረዳ **አርባጉጉ አውራጃ** ጋር አነግ ወጊያ ገጥሞ ብዙ ወታደር አልቆበታል። እኔ እራሴ ይላሉ አባ ኒቆዲሞስ፣ የ16እና የ17ዓመት ወጣት ሆኜ አገልግልና ውሀ ይዤ ከአያቴ ጋር የተካፈልኩበት ጦርነት ነው።በዚህ ጦርነት በእኛ በኩል የተመታው አስፋው ደሳለኝ የሚባል አንድ ሰው ብቻ ነበር። **ከእነሌንጮ ለታ** ጋር አብሮ የነበረውና ታዋቂ የቅርብ ሰው የምዕራብ ሐረርጌን **የአነግ ሠራዊት የመራው ሙህመድ በከሬ** የተባለው በዚህ ጦርነት ተገሏል። በዚህ ውጊያ አነግ ተሸነፈ።

እነኚህ አንጫርና አሰቦ ወረዳዎች ትጥቅ ሊያገኙ የቻሉበት ምክንያት 7000 የሚሆን የደርግ ወታደር ከአሰብ፣ከአፋር ወዘተ ካሉ ቦታዎች ቁጥጥር የሌለባቸውን መንገዶች በመከተል ወደናዝሬት ሲጓዝ ዘመናዊ መሣሪያውን በምግብ፣በልብስ፣በገንዘብ(በ50እና 60ብር) እየሸጠ የሲቪል ልብስ ለብሶ ወደዘመዶቹ ለመቀላቀል ሲሄድ ነበር።በዚህ ምክንያት በቂ ትጥቅ አገኙ።

**በ1984ዓ.ም መጨረሻ** ላይ ግን ያንን አካባቢ እንዲቆጣጠር በኢህአዴግ መመሪያ ሰጭነት ለኦህዴድ ተሰጠ።ኦህዴድም የኦሮሞን የበላይነት፣የአማራን የበታችነት አውጆ መጣ። የኦህዴድም መፈክር **"ነፍጠኛን ገረኢታ ጂቢቱስ ጃለልቱስ ኦሮሞ ጀለጉልታ--አንተ ቦርጫም አማራ ወደድከም ጠላህም ለኦሮሞ ትገዛለህ፣በኦሮሞ ሥር ትተዳደራለህ"** ይላል።አነግ እንዳደረገው ኦህዴድም የትጥቅ ፍቱ ጥያቄ ሲያቀርብ ተመሳሳይ መልስ አገኘ።ኦህዴድም ከገዥው ፓርቲ ጋር ሆኖ በሦሥት አቅጣጫ በከባድ መሣሪያ ጦርነት ከፈተ። በተለይ ሐምሌ 15ና 16ቀን 1984ዓ.ም ሪቡ ቀበሌ በተደረገው ጦርነት የታወቀው ጀግና የጎበዝ አለቃ ታደሰ ተገኝ ሲገደል ትልቅ ጉዳት ነበር።

ያም ሆነ ይህ እሥከ **1986ዓ.ም** ድረስ ይህ ሕዝብ ራሱን አሥከብሮ እየኖረ ባለበት ወቅት አረፍ ዓይኔ የተባለ ገዥውን ወክሎ ከአማሮች ጋር ተደራደረ።በድርድሩ መሠረት ከ1986 እሥከ1989ዓ.ም ሦሥት ዓመት አካባቢዎቹ በአማራው እንዲተዳደሩ ሆነ።በዚህ ጊዜ አማራው መሣሪያውን አሥረከበ።ከዚያ በኋላ ቀስ በቀስ አዘናግተው የኦሮሞዎች መስተዳድር ተጀመረ። በዚህ ጊዜ በአስቦ ወረዳ 34አማሮች ታሥረው የሞቱት ሞቱ፣ እነደመረው አበራም ከ15ዓመት እሥራት በኋላ ተፈተዋል፣የተሰደዱም ተሰደዋል፣በአንጫሮ ወረዳም እነ ዳኜ ልጇ ወርቅ፣እነአቻምየለህ አሰፋ፣እነ ደርቤ አሰፋ ወዘተ ተሰደዋል ።

አህዴድ ቂም በቀሉን በሚገባ ተወጥቷል። አነግንም አህዴድንም እንዲፈነጩብን ያደረገ ወያኔ ነው"።

## (2ኛ) <u>ምጽአተ ዐማራ</u>

አሁን በቅርቡ ደግሞ <u>በሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት</u> ተዘጋጅቶ ከወጣውና በገበያ ላይ ከዋለው **<u>ባለ 657 ገፅ "ምጽአተ ዐማራ" ከተሰኘው መፅሐፍ</u>** ለሌንጮ ከብዙ በጥቂቱ መልስ ከሚሆኑት ገፆች አጣቅሰናል።

(1) ገፅ 324 ጋራ ሙለታ(የሐረርጌ አንዱ አውራጃ) ከጥንት ጀምሮ በርካታ አማሮች ይኖራሉ።ወያኔና አነግ ግንቦት 20ቀን 1983ዓም ሥልጣን ከያዙ በኋላ በክረምቱ ወራት ዐማራዎች ጋራ ሙለታን ለቀው እንዲወጡ ውሳኔ አሥተላለፉ።ሐምሌ 18ቀን 1983ዓም ትጥቅ እንዲፈቱ ተደረገ። ሐምሌ 22ቀን 1983ዓም በዚሁ አውራጃ የነበሩ የኢሕአዴግ(ወያኔ) እና የአነግ ሠራዊት አባላት ምክንያቱ ለሕዝብ ግልፅ ባልሆነ ሁኔታ ጠብ ፈጥረው እርስ በርሳቸው ጦርነት ጀመሩ።

ነሐሴ 24ቀን 1983ዓም የአነግ ሠራዊት በጋራ ሙለታ የሚኖሩ ዐማራዎችን ቤት በነፍስ ወከፍ በመፈተሽ 32 ዐማራዎችን እንዲታሠሩ አደረገ።

ከዚያም የፍጥኝ አሥረው ከጋራ ሙለታ 18ኪሎሜትር ያህል ርቀት ካለው "ጅሌቻ" ከተሰኘው ገደላማ ቦታ ወስደው ዐይናቸውን ሸፍነው ከፍተኛ ጭካኔ በተሞላበት መንገድ በጥይት ደብድበው ገደሏቸው። ከአንድ ዓመት በኋላ አጥንታቸው ተለቅሞ "ዶጉ መድሃኒዓለም" ከተባለ ቤተክርስቲያን በጅምላ እንዲቀበሩ ሆኗል። ከተገደሉት 32 ዐማራዎች መካከል የ27ቱ ማንነት ታውቋል።ሙሉ ስማቸው፣ፆታቸው፣ነገዳቸው እና ዕድሜያቸው በሚገባ ዝርዝሩ አለን።

(2) ገፅ 326-327 ወተር በመጋቢት 1984ዓም በሐረርጌ የተፈፀመውን እልቂት ጋዜጠኞች ለአቶ አበበ ምትኬ ላቀረቡላቸው ጥያቄ ዕውነቱን ይናገራሉ። ይህን የሰማው **የአነግ አባልና የአካባቢው አስተዳደሪ** የሆነ ሰው የአቶ አበበ ምትኬን ዘጠኝ (9) ቤተሰብ አሥሮ ከእነነፍሳቸው **በደኖ** እንቁፍቱ ገደል ወርውሮ ጨረሳቸው።

በሐምሌ ወር 1984ዓም በዚሁ በወተር 48 ዐማራዎች ታርደው ተገድለዋል። 300አማሮችም ታሰሩ።

ለዚህ ዋና ምክንያቱ "ዐማራ" መሆን ቢሆንም፣ ወያኔና አነግ እንደገቡ ከጃራ እስላማዊ ኦሮሞ ቡድን ጋር አብረው መሥራት በመጀመራቸው "በደርግ ዘመን ጃራዎችን ያስይዙ የነበሩት አማሮች ናቸው" የሚል ነው።

በጃራ ይመራ የነበረው የእሥላማዊ የኦሮሞ ፅንፈኛ ቡድን በደርግ ጊዜም ሆነ በወያኔና ኦነግ ዘመንም ክርስቲያኖችንና አማሮችን ሲገድል ኑሯል፣እየገደለም ነው።

ያም ሆነ ይህ ወተር ለወራት ከታሰሩ በኋላ ኦነግ ከወያኔ ጋር ሲጣላ፣የያዛቸውን አማራዎች ወተር የተለያዩ አካባቢዎች ገደለ፣**ገሚሶቹን በደኖ** "እንቁፍቱ" ገደል ውስጥ ጨመራቸው።

ታስረው ከነበሩት የወተር 01 ቀበሌ ነዋሪዎች ገደል ተወርውረው የተገደሉት ሰዎች ሥም ዝርዝር በከፊል ይኸውና

1.መንገሻ ቦጋለ 2.ወርቄ አሸናፊ 3.ሙሉጌታ ትርፌ
4.ሲሳይ ተስፋዬ 5.ሽመልስ ኃይሌ 6.መምህር ዘውዱ ጨፍቅ 7.አለማዬሁ ዓምደብርሀን 8.የሽ ደስታ 9.ብርሀኑ አይፎከሩ 10.እንግዳ ዘገዬ
11.ዳኜ ወንድሙ 12.አበራ መንገሻ 13.ወይዘሮ ወርቄ 14. ታዬ በየነ
15.አባተ ወልደዬስ 16.ይልማ 17.ተሾመ መርሻ

ይህንን ግድያ የመሩት **እነጎች** 1.ዑጉምሳ 2.መገርሳ 3.ጫላ የተባሉ ናቸው።

በዚህ ወረዳ በዐማራው ሕዝብ ላይ ከተደረጉት በጭካኔነቱ ወደር ከማይገኝለት ዘግናኝ ግድያዎች መካከል አንዱ በእታፈራሁ ደጀኔ ላይ የተፈፀመው ነው። ይች ወይዘሮ በእህል ንግድ ሥለምትተዳደር ለፍታና ደክማ ያፈራችው ንብረትና ሀብት በገዳዮቿ እጅ እንደጣላት መረጃውን የሰጡ ሰዎች ያምናሉ።

በመጀመሪያ (ሀ)አሰሯት (ለ) ከዚያ ልብሷን አሥወልቀው አካላቷን አንድ በአንድ መቆራረጥ ጀመሩ (ሐ)ጡቷን ቆርጠው እንድትበላው አሥገደዷት (መ) ከመቀመጫዋ ላይ ሥጋዋን ቆርጠው ራሷ በራሷ እንድትበላው አደረጓት (ሠ) ብልቷንም እንዲሁ ቆራረጡት (ረ) በሰው ልጅ የመጨረሻ የሚባለውን ስቃይ አሰቃይተው ቆራርጠውና ከታትፈው ገደሏት።

(3)ገፅ 329 ከሐረር ከተማ 17ኪሎሜትር ርቀት ላይ ከምትገኘው ቀርሳ ቀበሌ 10 ዐማሮች በኦነግ ተይዘው መቃብራቸውን እየቆፈሩ እያሉ ዝናብ ሲመጣ ኦነጎቹ ለመጠለል ትንሽ ራቅ ሲሉ 2 ዐማሮች ለማምለጥ ሞከሩ። ብዙም ሳይርቁ ከያዟቸው በኋላ "ይህ የምታዩት ሰማዩም ምድሩም የእኛ ነው፣የት ነው የምታመልጡት፣ነፍጠኛ አማራ" በማለት ጭካኔ የተሞላበት ድብደባ ፈጸሙባቸው።

ይህ ወቅት ወያኔና ኦነግ እየተጣሉበት ያለ ወቅት በመሆኑና አማሮችንም ትረፉ ሲላቸው፣ ወያኔ ኦነጎችን ገሎ ለአማራው በተዘጋጀው ጉድጓድ አዳፍኗቸው ሄደ። ይህ የእግዚአብሔር ተዓምር ነው።

(4)ገፅ 344 አሰቦት ገዳም ክረምት ላይ 1983ዓም 16 መነኮሳትና አርድእት እጃቸው ታስሮ፣ ዓይናቸው ተሸፍኖ፣ በጀርባቸው ጥይት እየተኮሱ ወደፊት እንዲሮጡ በማድረግ "በኩርባ ጀርቲ ገደል" እየተምዘገዘጉ ወደቁ፣መሬት ሳይነካም ተንጠልጥሎ የቀረ አሥከሬን ብዙ እንደነበር የዐይን ምሥክሮች ይናገራሉ።

(5)ገፅ 345 **<u>በአርባ ጉጉ አውራጃ</u>** በአማራው ላይ ሥለተፈፀመው ወንጀል የምሥክሮች ቃል **<u>መስከረም 10 ቀን 1984 ዓም  ኦነግ</u>** መጣ።ዘሪሁን የሚባል በበቁሎ እየተመላለሰ የሚሠራ የአገልግሎት ሠራተኛ መንገድ ላይ በጥይት ተገደለ።

መስከረም 17ቀን በጀጁ ወረዳ አቡሌ ቀበሌ ገበሬ ማሕበር የአቶ እልፍነህ ጥግነህ 17 የቀንድ ከብቶች ተወሰዱ።በዚሁ ዕለት መርቲ ጀጁ ወረዳ ደግሞ አቶ እሸቱ የሚባል ከእነልጁ ተገደለ። የአማሮችን ሀብትና ንብረት መቀማት ቀጥሎና ችግሩ ተባብሶ መስከረም 29ቀን 1984ዓም የአቶ አበበ አክሊሉ ሚስትና ልጅ በጥይት ተመተው ልጃቸው ሲሞት ሚስታቸው ተረፉ።ጥቅምት 4ቀን 1984ዓም ወንጀሎ ቀርሳ ቀበሌ በአንድ ጊዜ ዘጠኝ (9) ሰዎች በጥይት ተደብድበው ሁሉም ተገደሉ።

**(3ኛ) ኦነግ** በአንድ ወቅት በሰጠው መግለጫ ላይ ሙሉ በሙሉ ድርጅቱ ኃላፊነት ባይወስድም የተወሰኑ ግለሰቦች ፈፅመውት ሊሆን እንደሚችል በ Human Rights Watch እንደተጠቀሰ ሌንጮ አይዘነጋውም።ታዲያ ሁሉንም ኦነግ አላደረገም ብሎ ሽምጥ መካድ ለምን አሥፈለገ?

ይህ በዚህ እንዳለ ኦነግ በትነግ ከተባረረ በኋላ በእነጦቢያ ፣በአሜሪካ ድምፅና በSBS በመሳሰሉት ያለውን እንከታተል፣

## <u>ጦቢያ ነሀሴ 17ቀን 1993ዓም</u>

-ኦነግ ከአነሳሱ "የኦሮሞ ሕዝብ በቅኝ ግዛት የተያዘ ሕዝብ ነውና ነፃ መውጣት አለበት"ባይ ነው።ከነፃ ኦሮሚያ በመለስ ድርድር ውስጥ መግባት "ለአበሾችና ለኢትዮጵያውያን መንበርከክና ማደር ነው" የሚሉ በአንድ ወገን ተሠልፈዋል።እነኚህም (1ኛ) ገላሳ ዲልቦ-የቀድሞ የደርግ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ|ቤት ካድሬና የኦነግ ዋና ፀሀፊ የነበረው (2ኛ) አቢዩ ገለታ-በእናቱ የጎጃም አማራ የሆነው፣ በደርግ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት የአሩሲ ክፍለ ሀገር ዋና አሥተዳዳሪና እሥከቅርብ ጊዜ ድረስም የኦነግ የውጭ ግንኙነት ኃላፊ የነበረው፣ (3ኛ) አባ ጫላ ለታ-የሌንጮ ለታ ወንድምና የኦነግ ሠራዊት አዛዥ የነበረ። እነኚህ "የኢትዮጵያ ጉዳይ አያገባንም ባዮች" ናቸው።

ሌላው ወገን ደግሞ “አቋማችን የዓለምንና የአካባቢያችንን ሁኔታ ያገናዘበ ሊሆን ይገባል። ለኦሮሞ ሕዝብ ብዛትና ሀብት የሚመጥን ቦታና መብት ለኦሮሞ ሕዝብ ከተሰጠ፣ከቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር መኖር የማይቻልበት ምክንያት የለም” የሚለው ቡድን አመራሩን ይዟል።በዚህ ቡድን ውስጥ (1ኛ) አባ ቢያ-በ1966ዓ.ም ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ጅማሮ ላይ የከፋ ዋና አስተዳዳሪ  የነበረው( 2ኛ)ሌንጮ ባቲ-የውጭ ግንኙነት ኃላፊው (3ኛ) የአሁኑ ፀሀፊ ዳውድ ኢብሳ ይገኙበታል።

## <u>የአሜሪካ ድምፅ</u>

**<u>2005ዓ.ም</u>**(በጎርጎሳዊያን|ግሪጎሪያን 2012) ታህሳስ መጨረሻ  ላይ **ቦሩ በረካ <u>አነግን</u>** ወክሎ በአሜሪካ ድምፅ እንዲህ አለ ”ከመገንጠል ውጭ አማራጭ የለም ይልና፣እንደኦሮሞ ብናስብ ፣ይህን የመሰለ ብዙህን ሕዝብ፣ይህን የመሰለ የኢኮኖሚ ጀርባ የሆነ አገር እያለን፣በቆዳ ሥፋትም በጣም ሠፊው ክልል ሆኖ እያለ፣ሁልጊዜ የኦሮሞ ሕዝብ ወደጎን የተገፋ ነው” ብሎናል።የአነግ አቋም ያው እንደጥንቱ ነው።

## <u>SBS</u>

2007-8ዓ.ም(በግሪጎሪያን|ጎርጎሳዊያን 2014) **<u>የአዴግ ሰዎች</u>** በ SBS ተጠይቆ እነ ሌንጮ ባቲ ደግሞ <u>“ኢትዮጵያ እንደአገር አንድነቷ ተጠብቆ በሰላም ልትኖር የምትችለው  ፌደራል(የጎሳ)</u> የሆነ ሥርዓት ውስጥ ሥትተዳደር ነው የሚል አመለካከት አለን ።ይህ ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ የማንነት የፖለቲካ ጥያቄ ሥላለ መልስ ሠጥተን፣የተለያዩ ብሔር|ብሔረሰቦች ቋንቋቸውን የማስከበር፣የፖለቲካ መብታችውን የመጠቀም፣የተፈጥሮ ሀብታቸው ላይ የማዘዝ፣ ራሳቸውን በራሳቸው የማሥተዳደር፣ከሌላ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር ደግሞ አብሮ የሚያስተዳድራቸው የፌደራል አወቃቀር እንዲኖራቸው ነው የምንመኘው”ካለ በኋላ፣ የኢትዮጵያ  አሥተዳደር “በብሔሮች መዋቀሩ ትክክል ነው፣ባለው ህገ መንግሥት መታገል እንችላለን” ብሎናል።

<u>ጠያቂው</u> አሁን እንዳለው ቋንቋን መሠረት ያደረገ ፌዴራሊዝም  ነው ወይስ እንደአሜሪካና አወስትራሊያ ዓይነት ብሎ ይጠይቃል?

<u>ሌንጮ ባቲ</u> ሲመልስ ይህ አሁን ያለው ቋንቋን መሠረት ያደረገ ፌዴራላዊ አወቃቀር ትክክለኛ ነው።ግን ዲሞክራሲያዊ ሥላልሆነ የፖለቲካ ችግሮች እየታዩ መጥተዋል።

<u>ጠያቂው</u> አዲስ አበባን በተመለከተስ ብሎ ይጠይቃል?

<u>ሌንጮ ባቲ</u> ሲመልስ ፊንፊኔ ላይ ከሰሜን መጥቶ የራሱን ባህል አስፋፍቶ ኑሯል፣የኦሮሞ ነች፣የፌዴራል ከተማ ነች።በታሪክ ባለቤትነት የኦሮሞም ዋና ከተማ ሆናለች።

**ልብ ያለው ልብ ይበል!** እነኚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የኦነግና የኦዴግ ልዩነቶች፣ልዩነቶች ሳይሆኑ አነጎች ካለው ከኢትዮጵያ ሁኔታ በመነሳት ለአንድ ዓይነት ግብ ሁለት የተለያዩ የታክቲካ አካሄዶችን በመጠቀም፣ሥነ ልቦናችንን ጠንቅቀው ሥለተረዱት፣በሌሎቻችን ላይ የተለያዩ ጫናዎችና የማደነጋገሪያ ሸወዳ በማስቀመጥ የሚፈልጉትን ነገር ተግባራዊ ለማድረግ  ነው።ከሦሥት ዓመት በላይ ያስቆጠሩት <u>ኦነግ እና ኦዴግ</u> ብለው አንድ ዓይነት ግብ ያላቸው፣ነገር ግን ሁለት ሥም ያላቸው ድርጅቶች ሌላውን ህብረተሰብ ግራ በማጋባትና እርስ በርሱ በመከፋፈል  ድጋፍ ለማሰባሰብ ጭምር፣በሁለት አቅጣጫ  ብቅ ብለው ግንጠላውን ሲያፋጥኑ ይስተዋላሉ።

ኦነግ ነኝ ባዩ <u>**ቡሩ በረካ**</u> የሚለን <u>**ብዙ ሕዝብ፣ሠፊ መሬትና ሀብት ያለን**</u> ሆነን ሥለተገፋን እንገነጠላለን ይለናል።ባንዲራውም በየሰላማዊ ሰልፉና በየስብሰባው የምናየው ነው።

ኦዴግ(ውስጡ ኦነግ የሆነ  ልብ ሊያማልልና ሊያታልል ካባውን ገልብጦ የመጣውን)ድርጅት የሚመሩት የኦነግ መሥራቾች እነሌንጮ ለታ፣እነዲማ ነጎ፣እነሌንጮ ባቲ ወዘተ ናቸው።ዲማ ነጎ ከዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ ጋር በአሜሪካ ድምፅ ቃለምልልስ ቀርቦ ሥለባንዲራው ተጠይቆ ሲመልስ ባንዲራችን ከኦነግ ጋር አንድ ነው ብሏል።ሁለት የተለያዩ ድርጅቶች ሆነው አንድ ዓይነት ባንዲራ መጠቀም በራሱ ያላቸውን "አንተ በዚህ ሥራ እኔ በዚያ ልሥራ "የሚል ውሥጣዊ የታክቲክ አሠራር እንጅ፣የእነርሱም አቋም **"የጎሳን ፌዴራሊዝም መሠረት ያደረገ <u>ለኦሮሞ ሕዝብ ብዛትና ሀብት የሚመጥን ቦታና መብት ለኦሮሞ ሕዝብ ከተሰጠ</u>** ከቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር መኖር የማይቻልበት ምክንያት የለም"ነው።  ጥያቄው ግን ካልተሰጠስ ወይም እንደሚመኙት ካልሆነስ  ነው? ጦርነት ሊከፍቱ ነው ወይስ ሊገነጠሉ?

ለእነኚህ ድርጅቶች ተራው የኦሮሞ ሕዝብ  ድጋፉን  ይሰጣል ወይስ አይሠጥም።ጊዜ ያሳዩናል።

**ኦሮሞዎች ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣታቸውና ከመውረራቸው በፊት የነበሩ የቦታ ሥሞችና አሁን የሚጠሩበት ሥም በከፊል፣**

| **የጥንት(ነባር) ሥም** | **በጋላ(በኦሮሞ) የተሰጠ ሥም** | **ነባርና ነዋሪ ነገዶች** |
|---|---|---|
| ፈጠጋር | አርሲ፣ሲዳሞና ጎምጎፋ | ዐማራ፣ሜያ፣ አዳል፣ሀዲያ፣ጉራጌ |
| ደዋሮ | ሐረርጌ | ሀዲያ፣ከምባታ፣ዐማራ፣ጉራጌ |
| እንዶጥና | ጉለሌ፣የካ፣ፊንፊኔ፣እንጦጦ(አዲስ አበባ) | ሜያ፣ ዐማራ |

| | | |
|---|---|---|
| ግራርያ | ሰላሌ | ዐማራ፣ሜያ |
| እንደገብጣን | ሜታ | ዐማራ |
| ቤተ አማራ(ገነቴ) | የጁ | ዐማራ |
| አንጎት | ራያ | ዐማራ፣አገው |
| ላኮ መልዛ | ወሎ | ዐማራ፣አዳል |
| መካነ ሠላም | ቃሉ | ዐማራ |
| ሠገነት | ወረሂመኖ | ዐማራ |
| ዋስል(ቤተ ጊዮርጊስ) | ወረኢሉ | ዐማራ |
| ቤተሳባ | ወረባቦ | ዐማራ |
| ቢዛም | ቄለም(ምዕራብ ወለጋ) | ዐማራ፣ጋፋት፣እናርያ፣ አንፈሎ |
| ዳሞት(የጊቤ ወንዝንና የዛሬውን ጎጃም ይጨምራል) | ጎጃም፣ሌቃ(ምሥራቅ ወለጋ) | ዐማራ፣ ጋፋት፣እናርያ |
| ዝሆን ጆሮ | የረርና ከረዩ | ዐማራ፣ሜያ፣ ሀዲያ፣ከምባታ |
| ላሎ ቅሌ | ኢሉባቡር | እናርያ፣አንፈሎ |
| ገሙ | ጂማ | ዐማራ፣ጃንጃሮ |
| ባሊ | ባሌ | ዐማራ፣ሜያ |
| | | |
| ገንዝ | ጅባትና ሜጫ | ዐማራ፣ሜያ፣ሀዲያ፣ከምባታ |
| ወጂ | ውንጂ | ዐማራ |

## <u>ዋቢ መፃሕፍት</u>


ይልማ ደሬሳ የኢትዮጵያ ታሪክ በ16ኛው ክፍለ ዘመን፣ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1959ዓ.ም

ተክለፃዲቅ መኩሪያ የግራኝ አህመድ ወረራ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1966ዓ.ም

ሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት ምጽአተ አማራ ዋሽንግተን ዲሲ 2009ዓ.ም

ሚጉኤል ዴ-ካስታሆንዝ የፖርቱጋሎች ጀግንነ ት ተርጓሚዎች ዶክተር ሙራድ ካሚልና አቶ ዮናስ ቦጋለ፣ተሰፋ ማተሚያ ቤት አ.አ.1952ዓ.ም

ጦቢያ ኦነግ አ.አ. ነሐሴ 17ቀን 1993ዓ.ም.

አባ ኒቆዲሞስ አሰፋ በኢሳት ቃለ ምልልስ

ቦሩ በረካ (የኦነግ አመራር) በአሜሪካ ድምፅ ቃለ መተይቅ 2005(በጎርጎሳዊያን|ግሪጎሪያን2012)

ሌንጮ ባቲ(የኦዴግ አመራር) በSBS ቃለ መጠይቅ 2007-2008(በጎርጎሳዊያን|ግሪጎሪያን2014)ዓ.ም Alvarez, Francisco: Verdadeira Informacao-የግራኝ አህመድ ወረራ በተባለው የተከለ ጻዲቅ መኩሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተተረጎመ።

Conti ,Rossini: Storia di Etiopia,Corpusco 1958 Liber Axume Corpusco 1962

Cerulli ,Enrico: Studi Etiopia-Storia di Harar

Bassett, Rene: Etudes Sur L΄histoire d΄Ethiopie(ከአረብ ፋቂህ አብደል ቃድር መፅሐፍ ተወስዶ በዚህ መፅሐፍ ወስጥ የተተረጎመ)

Guidi ,Ignazio: Histoire genti Galla, Corpusco,Louvian, 1960(በ1530ዎቹ አባ ባሕርይ ሥለኦሮሞዎች አመጣጥ በግ ዕዝ በ እጃቸው የፃፉት ማስታወሻ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ተተርጉሟል)

Manroe, Jones: Histoire de L΄Abissinie, 1936 Roma

Pereira, E : Chronica de Susenyos,Corpusco,1962

**ማሳሰቢያ**! ወያኔና ኦነግ ከአገሪቱ መሬት የዝሆን ድርሻቸውን ወስደው አማራውን እርቃኑን ካስቀሩ በኋላ “የኦሮሞ ሕዝብ ብዛት አለው፣ሀብቱም ተዝቆ አያልቅም፣ክልሉም ሰፊ ነው፣ በዚያው ልክ ተጠቃሚ መሆን አለበት ይህ ካልተደረገልን የኢትዮጵያ አንድነት አይታሰብም ሲል የነሌንጮ ቡድን፣ኦነግ ደግሞ እንገነጠላለን የሚሉትን የልጆች ማስፈራሪያ አንግበዋል። ይህንን ከገፉበት፣አለቃ ገብረ ሀና **“እዚያም ቤት እሳት አለ”** እንዳሉት፣ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ሥሞች ወደቀድሞው ሥማቸው መመለስ እና ነባር ነገዶችም የባለቤትነት ቦታቸውን መልሰው መያዝ ይኖርባቸዋል።ለዚህ ደግሞ የሚከፈለው መሥዋዕትነት ተከፍሎም ቢሆን ይሆናል እንጅ ወያኔና ኦነግ የሸነሸኑትን ተቀብለን አንኖርም።ይህ ሲሆን የሚኩራሩበት ሀብትም ክልልም እና የሕዝብ ብዛትም ይመናመናል፣ምክንያቱም የሌሎችን ቦታና ሀብት ሥለወሰዱ፣የኦሮሞ ሕዝብ የሚባለውም በግዳጅ የተያዙትም የተለያዩ ነገዶች ሲለዩ ይኮሰምናል። ከዚያ በኋላ ሁላችንም ልካችንን እናውቃለን።

“የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ” እንደሚባለው የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በምንግባባበት መንገድ መግባባታችን አይቀሬ ነው።

የወያኔ ትግሬዎች ላይ **ማተኮር** ሲገባ ለምንድነው ሥለአነግ የሚነሳው የሚሉ ተችዎች ካሉ መልሱ “የወያኔ ትግሬዎች የአማራውን ዘር ለማጥፋት ቀደም ሲል በሥውር አሁን ደግሞ በግልፅ ጦርነት ሥለአወጁበት፣አማራው በወያኔ ትግሬ ላይ **ከማተኮር አልፎ፣ የሞት የሽረት ትግል** ሥለሚያካሂድ **በአማራው ላይ ያተኮራችሁ** ተችዎች ከአማራው ራስ ወርዳችሁ በወያኔ ላይ እንድታተኩሩ ምክሬን እለግሳለሁ። በኤርትራ ያሳዬነውን ንዝህላልነት በተመሳሳይ ሁኔታ በእነአነግና በመሥራቾቹ ሊደገም ዳዴ ሲል በመገንዘባችን “ከኋላ ወየው ጠንቀቅ ብለህ ቆየውን” መምረጣችን የግድ ነው።

መታወቅ ያለበት ጉዳይ **አብሮ በመኖር ሁሉም ተጠቃሚ ነው፣በመለያየት ሁሉም ተጎጅ ነው፣** አማራው! ይህንን ጠንቅቆ በመረዳቱ ያላንዳች መታከት፣ተቻችለን እንኑር ብሎ እየሞተም ለምኗል፣አሁንም ቢዘገይም ተሚጦ አላለቀምና አብሮና ተሳስቦ ለመኖር ማንኛውም ነገድ ያስብበት።ወያኔም ተለምኖ ነበር፣ልመናው ለኢትዮጵያ አንድነት ሲባል ነበር፣ግን እንደፍርሀት ቆጠረው። የግፉ ፅዋም ሞልቶ ሲፈስ ውጤቱ እንደምናየው ሆኗል። ከእንግዲህ የፈጀውን ጊዜ ይፈጃል እንጅ  አንላቀቅም። ከትግሬ ጋር አብሮ መኖር የሚያከትም ከሆነ፣የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ከተከዜ ወዲህ ብቻ ሳይሆን ከተከዜም ወዲያ እሥከ አምባላጌና ማይጨው ያለውን መሬታችንን እናስመልሳለን።

የኢትዮጵያ አንድነት የተደመሰሰውና የጠፋው ወይም ያለቀለት የትግሬ ወያኔዎችና አነግ በሽግግር መንግሥት ተብዬው 1983ዓ.ም ተሰብስበው አገሪቱን ሲሰነጣጥቁና ሕዝቡንም ሲያመሰቃቅሉት ነው።ይህም አካሄዳቸው፣አፈፃፀማቸው፣ከህገ መንግሥቱ አንቀፅ 39 ጀምሮ በጎሳ እሥከመሸንሸን  መድረሳቸው  ቁልጭ አድርጎ የሚያሳዬን  ቢለዋ እንደተሳለልን ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ  አማራው ለእርድ እንደቀረበ ክቡር አሥራት ወልደዬስ ቀድሞ ሥለገባቸው ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን መዐሕድን በማቋቋም የእሳት አደጋውን ለማጥፋት ሲጥሩ፣ ከትግሬው ወያኔ ባልተናነሰ መልኩ ራሱ አማራ ነኝ ባዩ ጭምር ፀረ-አማራነትን በማሥተጋባት ታገላቸው፣ታገለን። እኛም በየአገሩ የነበርን ወገኖች ጥቂትም ብንሆን “አማራ ብሎ መነሳት ዕብደት ነው” እያለ የገዛ ወገናችን የጭቃ ጅራፉን ቢያጮህብንም ምንም ሳይበግረን እሥከቻልን ብንጥርም ሁሉም ነገር ከፕሮፌሰር አሥራት ጋር አረፈ።

አማራው ወገናችን በአማራነት አልደራጅም ብሎ የራሱን ድርጅት አፍርሶ፣ በምኞትና በፍላጎት ብቻ ታጥሮ በተጨባጭ የሌለንና ያለቀለትን የኢትዮጵያን አንድነት መፈክር ይዞ ሲንዘባዘዝ፣ጠላት ያለማቋረጥ ለ25ዓመታት  በአማራነት እየመረጠ ሲቀጠቅጠው፣

ሲያባረው፣ ሲያጠፋውና ሲገለው ኖረ።ይህን ሁሉ ዓመታት ጠላት ለመጠናከር እና ብዙ ነገር ለማውደም ጊዜ ከማግኘቱም በላይ፣አማራውን በአማራነት እየገደለው በኢትዮጵያ አንድነት መንገዛገዙ፣ ቀሪውን አማራ ከማስጨረስና የአማራውን ሠቆቃ ከማራዘም በስተቀር መፍትሄ እንደማያመጣ የተረዳው፣ትናንት ከእርሱ አብራክ የወጣው ወጣት አማራነቱን አጉልቶ ብቅ ሲል የተሰማኝ ደስታ ወሰን የለውም።ሥመኘው የኖርኩትም አማራው ለማንነቱ ቆርጦ ሲነሳና ሲታገል ማየት ነበር። እደግ ተመንደግ እለዋለሁ።እኔም እሥከህይወቴ ፍፃሜ ከጎኑ ነኝ።የሞረሽም ያልተቋረጠ የቅስቀሳና የማንቂያ ሥራዎች ተግባራዊ ሆነዋል፣የሚያስመሰግነው ነው።አማራ ብለው ለተነሱት የአማራ ድርጅቶችም ሆነ ግለሰቦች አክብሮታችን ትልቅ ነው።በተለይ ደግሞ አሁን እንደጀመራችሁት ተቀራርባችሁ አንድነታችሁን እያጠናከራችሁ በሄዳችሁ ቁጥር ሁላችንም እንደአንድ ሰው ማሰብ እንጀምራለን፣ጊዜውም ሩቅ አይደለም።

***መደምደሚያ***! የአማራ **ማንነቱ** በወያኔ ትግሬዎችና በሌሎች ፀረ-አማራ ኃይሎች ሥለተካደና ሲያጠፉት ሥለሚቅነዘነዙ እንዲሁም የመኖር ዋስትናውና ህልውናው አጠያያቂ በመሆኑ የራሱን ማንነት ለማሥከበር ቆሟል። <u>አማራው ዛሬ ከምድረ ገፅ ከመጥፋቱ በፊት ለራሱ ህልውናና ለማንነቱ ብቻ እንደሚዋደቅ መታወቅ አለበት።</u>ይህም መብቱ መሆኑን መቀበል የግድ ነው። ይህንን መብቱን ለማስከበር ሲታገልና ሲዋደቅ ችግሩን ተረድተው ከጎኑ ከመቆም ይልቅ፣ ቀደም ሲል እየተጠቃና ሳይገል እየሞተ በተጓዘበት መንገድ እንዲቀጥልና እንዲያልቅ የሚመኙ ካሉ ምኞት ብቻ ሆኖ ይቀራል።

በአማራው ላይ ግፍ የሠሩና የሚሰሩ የዘር ቡድኖችን እያቀማጠሉ፣(1) "አማራው በአማራነት መቆሙ ወያኔ በቀደደው ቦይ መፍሰስ ነው" ለሚሉት ጠላቶች መልሳችን "ያረጀ ያፈጀ የማዘናጊና ትጥቅ አስፈች ንግግር ስለሆነ ተቀባይነቱ አክትሟል" ነው፣ (2) **<u>"አማራውን አክራሪ"</u>** ሆኗል ለሚሉት ኃይሎች፣አማራው ሞቶ እነርሱ መኖር የሚመኙና ከወያኔ ለይተን የማናያቸው ጠላቶች ሥለሆኑ፣መልሳችን **<u>"የከረረው ይበጠስ"</u>** ነው።

ከእንግዲህ አማራው አምርሯል፣የጀመረውንም ከፍፃሜ ሳያደርስ እንደማይቆም እቅጩን አውቆ አብሮ መቆም ነው፣ አለዚያ ከአማራው ራስ ወርዶ አርፎ መቀመጥ ወይም የራስን ሥራ መሥራት ነው።

**ለግንዛቤ ያህል!** ጋሎች(ኦሮሞዎች) የኦሮሞ ሥሞች ያሉባቸውን ቦታዎች፣የእኛ የሚሉት አባዜ ውስጥ መግባታቸውን ዛሬ ላይ ቆሜ ሳየውና ሥመለከት፣በግራኝ ወረራ ከደቀቀና ከተዳከመ የአማራ ጦር ጋር ገጥመው አማራ በብዛት በሚኖርባቸው አካባቢዎች ከተሸነፉ በኋላ፣ብዙ በሥማቸው የቀየሯቸውን የኦሮሞ ሥሞች ለምን አማራው እሥከዛሬ ወደጥንት ሥማቸው አልቀየረም የሚል ቁጭት ቢያድርብኝም፣

አማራው በባህሉ አብሮነትን እንጅ ሥም ላይ እንደነሱ አለመንጠልጠሉንና ሥም ወደመቀየር አለመሄዱን ሳጤን ትልቅነቱን እረዳለሁ። ከእንግዲህ ወዲህ እኛ በጥንት ሥሞቻቸው መጥራትን እንጀምራለን።

**አያሌው ፈንቴ**